የቤተክርስትያን
ሕግጋት
በአዲስ ኪዳን

ዶ/ር ጊተር ማስተርስ
ጆን ፍሪቸር ቤንጃሚን ኪች

ትርጉም ፓስተር ኃይለስላሴ ተፈራ

የቤተክርስትያን ስባሰነት
በሰዲስ ኪዳን

© Peter Masters 1981

የአማርኛው የመጀመሪያ እትም 2005

Wakeman Trust
38 Walcot Square
London SE11 4TZ
United Kingdom
Email: books@wakemantrust.org
ISBN 1 870855 49 3
ISBN 978 1 870855 49 5

የሽፋን ዲዛይን አንድሩ ኦወን

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ በሙሉ ያለአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ በማናቸውም መንገድ ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው::

Printed by SIM Printing Press, Addis Ababa, Ethiopia.

ማውጫ

ገፅ

1 መጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተክርስትያን አባልነት 5

2. የአጥቢያ ቤተክርስትያን ባሕርያት 14

3. የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ 22

4. የቤተክርስትያን አባልነት ሕግጋት 29

5. የቤተሰብ ቃል ኪዳን 33

መጽሐፍ ቅዱሳዊው
የቤተክርስትያን አባልነት

የቤተክርስትያን አባልነትን በተመለከተ በማያጠራጥረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ መመሥረታችን በጣም ጠቃሚ ነው። ሆኖም የቤተክርስትያን አባልነትን አስፈላጊነት የማይቀበሉ አንዳንድ ቅን አማኞች አሉ። ሌሎች ደግሞ ሕይወት ያለው አባልነት ወይም አገልግሎት በሌላቸው ቤተክርስትያናት ውስጥ አባላት ናቸው ወይም ባሉበት ቤተክርስትያን በሚሰጠው ትምህርት ሙሉ በሙሉ አይስማሙም። ስለዚህ የቤተክርስትያንን አገልግሎት ከመደገፍ ወይም ከቤተክርስትያን ጋር ከመተባበር እጅግ በጣም የራቁ ናቸው። አሁንም ደግሞ ሌሎች ትርጉም ላለው አባልነት ራሳቸውን ሳይሰጡ ዓመታትን እያሳለፉ ናቸው።

በውስጥ እና በውጭ ያሉ

ስለቤተክርስትያን አባልነት የእግዚአብሔር ቃል ምንድነው የሚለው? የአዲስ ኪዳን ጊዜ አማኞች ከአንድ ነገር ጋር ጎብረት ወይም አንድነት ፈጥረው ነበርን? በጣም ብዙ የአዲስ ኪዳን አንቀፆች ጥያቄውን በግልፅ ይመልሱታል። በአዲስ ኪዳን ጊዜ አጥቢያ ቤተክርስትያንን የምናገኛት እንደ አንድ ልዩ አንድነት ወይም መንፈሳዊ ቤተሰብ አንድ በመሆን ተተርጉማ በእግዚአብሔር ተቀይሳና አንድ ለመሆን ታቅዳ ነው። በመሆኑም የሷ የሆኑ ሁሉ ለሕይወቷና ለሥርዓቷ ቃል የገቡና የተሰጡ ናቸው።

በመጀመሪያ ከ1ቆሮ5:4-6 ላይ የምንማረው የመጀመሪያው መቶ ዓመት አጥቢያ ቤተክርስትያን በሚገባ የተቋቋመች እርምተ ቤተክርስትያንን (ሥርዓተ ቤተክርስትያንን) ለመጠቀም ኃይል የነበራት ማኅበረ-ሰብ (ኮሙኒቲ) የነበረች መሆኗን ነው። (በዚህ ክፍልም ላይ ያለው በዝሙት የተገኘውን ከቤተክርስትያን መካከል ስለማስወገድ ነው) «***ይህን እንደዚህ በመፈው ሳይ በጊታችን በሲየሱስ ክርስቶስ ስም ስሁን ፈርጂዐታለሁ እናንተና መንፈሱም ከጊታችን ከሲየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን መንፈሱ በጊታ በሲየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ሰሥጋው ጥፋት በሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዱ ነው።።***»

የቤተክርስትያንን አባልነት መርሆ በማስረዳት በኩል ይህ ጥቅስ በመጀመሪያ ሲታይ ከባድ ይመስላል። ነገር ግን በከፍተኛ ኃጢአት በደለኛ የሆነን አንድ ሰው ከጎብረታቸውና ከእድሉ ለማግለል የአማኞች ልዩ የሆነ ስብሰባና ያላቸው ኃይል ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ስለሚገልፅ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው። የአማኞች ልዩ ስብሰባው ዝም ብሎ ጉባኤ ወይም ለሕዝብ ሁሉ ክፍት የሆነ ስብሰባ አልነበረም። በቆሮንቶስ ቤተክርስትያን የነበረው ክፍት ጉባኤ የማያምኑትን፣ ተጠራጣሪዎችንና ጌታን ለመቀበል

አዲስ የመጡትንም ሁሉ ይጨምር ነበር። (1ቆሮ14:24-25 የሚያሳየው በቆሮንቶስ ቤተክርስትያን መደበኛ የሕዝብ ስብሰባ ላይ የማያምኑም ሰዎች ይሳተፉ እንደነበር ነው)። ኃጢአተኞችና የማያምኑት ከክርስትያን ስብሰባ ሊገለሉ አይገባም እንዲህ ከሆነ ማንም የጌታን ቃል ሰምቶ ሊድን አይችልምና።

ሆኖም የቆሮንቶሱ ኃጢአተኛ ለሰይጣን አልፎ ተሰጥቷል ማለትም ከመንፈሳዊው ጎብረት በረከትና መጽናናት ተወግዶ ወደ ዓለም እንዲመለስና ከቤተክርስትያን ውጭ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም የተደረገው እሱ ወደ ማስተዋል እንዲመለስ ደግሞም የቤተክርስትያንን ንጽህና ለመጠበቅ ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ቆሮ5:12-13 ላይ የሚከተሉትን ቃላት ተናግሯል:- «***በውጭ ባሉ ሰዎች ላይ መፍረድ ምን ያገባኛ? በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ትናንተ ልትፈርዱምን? በውጭ ባሉት ላይ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።***»

በውስጥ ያሉት? ... በውጭ ያሉት? ... በውስጥ ያሉት ወይም በውጭ ያሉት ... ... ምን? የቤተክርስትያን ክፍት ጉባኤ ተካፋዮች ወይስ የቤተክርስትያን አባላት? ይህ ዓይነቱ ቋንቋ ሊጠቅስ የሚችለው በትክክል የቤተክርስትያን አባላት የሆኑትንና የተለወጡትን ሰዎች ብቻ ነው። በክርስትያኖች ባሕርይ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ሥልጣን ኖሮት መፍረድ የሚችለው እንደዚህ ዓይነቱ ጎብረት ብቻ ነውና።

በአዲስ ኪዳን ጊዜ በጣም ግልፅ የሆነና የተወሰነ የሰዎች ክልል ወይም መቀራረብ ነበር። ያም በጥብቅና በጥንቃቄ የተደነገገ ስለነበር አንድ ሰው ሊሆን የሚችለው በዚያ ክልል ውስጥ ወይም ከዚያ ውጭ ብቻ ነበር። ስለዚህ በዚያ ክልል ውስጥ የነበሩት ሰዎች ለዚያ ማኅበረ-ሰባቸው ወይም ኮሙኒታቸው ለሥርዓቱና ለፍርዱ በፈቃዳቸው ራሳቸውን ሰጥተው ነበር። ከዚህም እውነት የተነሳ ከዚያ በኋላ ብቸኞች አልነበሩም።

ለሥነ ሥርዓት የተቀናጁ

በአጥቢያ ቤተክርስትያን መኖር ስለሚገባው ትክክለኛ የአባላት መዋቅር አስፈላጊነት በማቲዎስ18 ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአማኞች መካከል ስለሚነሣ መበዳደል አስመልክቶ በሰጠው አጠቃላይ መመሪያ ላይ ይታያል። ይህ ምዕራፍ በደልን አስመልክቶ ማድረግ የሚገቡንን ዝርዝር ሂደቶች አያስተምርም (ይህ በመልክቶች ላይ ተዘርዝሯል)። ክፍሉ የሚገልፀው መመሪያ በጌታ ሕዝብ መካከል መበዳደል በሚከሰትበት ጊዜና ይህንንም ራሳቸው ሊፈቱት ካልቻሉ ጉዳዩ በቤተክርስትያን ይፈታል የሚለውን ነው። ጥፋት ፈጻሚው ወይም በዳዩ ቤተክርስትያንን አልታዘዝም ካለ ከጎብረት በመታገድ እንዲሰቃይ ይደረጋል እንደ ቀራጭና እንደ አረመኔ ይሁንልህ ይላልና።

በዚሁ ምዕራፍ ላይ ጌታ ኢየሱስ ለአዲስ ኪዳን አጥቢያ ቤተ ክርስትያን የሚከተለውን ኃላፊነት ሰጥቷል። «***በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።***» (ማቲ18:18)።

ይህም ቤተክርስትያን ነፍስ የማዳን ሥልጣን አላት ማለት አይደለም። ነገር ግን በዚህ ዐውድ ውስጥ ቃሉ የሚያስተምረው ነገር ቢኖር አጥቢያ ቤተክርስትያን (እርምት ቤተክርስትያን በጽድቅ መደረጉን በማሰብ)

ከባድ በደል የፈጸመውን ከአባልነት ማገድ ሲኖርባት፣ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርም ይህንን የቤተክርስትያን ውሳኔ በሰማይ ሆኖ ይደግፈዋል የሚለውን ነው። በደለኛው በእውነት የዳነ ከሆነ ደጎንነቱን አያጣም። ሆኖም ጌታ አግዚአብሔር በበኩሉ የበረከት እጁን ከሱ ላይ ያነሳል እናም ወደ ንስሐ እንዲመጣ ይገሥጸዋል። እርሱም ሕዝቡ በምድር ላይ እንዲፈፅሙ የሰጣቸውን ትዕዛዝ ሲያከናውኑ የወሰኑትን ውሳኔ አይቀይርም ወይም ያንን ውሳኔ አይሽርም።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥቢያ ቤተክርስትያን እጅ ውስጥ ሥልጣንና ኃላፊነትን አስቀምጧል። ይህም አጥቢያ ቤተክርስትያን ቋሚ፣ የታወቀች፣ የተደራጀችና ሥርዓት ያለው ማኅበረ-ሰብ እንድትሆን እንጂ፣ ዝም ብሎ ቅርፅ የለሽ እና የታወቀ አባልነት የሌላት ሆና እንድትቀጥል አይደለም።

አንድ አጥቢያ ቤትክርስትያን መደበኛ አባልነት የሌላቸው ዝም ብሎ የምዕመናን ስብሰባ ከሆነች በውስጧ በእውነት ያልዳኑ እንዲሁም ብዙ የተ ሞኙ ተሳታፊዎች ወይም አስመሳይ ተመላላሾች ይሞሉባታል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት ለታይታ የሆነ መንፈሳዊ ሥራ ክርስቶስ ለቤተ ክርስትያኑ ሰጥቶ አያውቅም።

በኢየሩሳሌም የነበረችውን ቤተክርስትያን መደባለቅ

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ከአጥቢያ ቤተክርስትያን ጋር ኅብ ረት ስለ ማድረግ ወይም ስለመደባለቅ ጠቃሚ ማስረጃዎችን እናነባለን። ከነዚህም ውስጥ በጣም ጠቃሚው ምሳሌ በሐዋ9:26-28 ላይ ያለው ነው።

«ሳውሎስም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀመዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ ሁሉም ደቀመዝሙር ስንደሆነ ስላመኑት ፈሩት። በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት ሰገባውና ጌታን በመንገድ ስንዴት ስንዳየውና ስንደተናገረው በደማስቆም በኢየሱስ ስም ደፍሮ ስንዴት ስንደተናገረ ተረከላቸው።»

---

*በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተክርስትያን አባልነት ፅንሰ አሳብ የማያምኑ ክርስትያኖች፣ በቆሮንቶስ ላይ ያለውን ዓይነት የእርምተ-ቤተክርስትያን ቃል የሚረዱበት የተለየ አቋም ወይም መመሪያ ሊያዘጋጁ ይገባቸዋል። እነዚህንም መተርጎም ያለባቸው የጌታን ራት መካፈልን መከልከል እንደሆነ አድርገው ነው። እነሱ እንደሚሉት ከሆነ «ኃጢአተኛውን ሰው ማስወገድ» የሚለው ቃል የሚገልፀው የጌታን ራት እንዳይካፈል ብቻ ስለመከልከል ነው።

ሆኖም ሐዋርያው ስለጌታ እራት ቢጠቅስም እንኳን የተናገረው እንደ አንድ የትእዛዝ ክፍል ብቻ ሆኖ ነው። አስወግዱት የሚለው ትእዛዝ (1ቆሮ5:7) የሚገልጸው አንድ ሰው የጌታን ራት እንዳይካፈል መከልከልን ብቻ ሳይሆን ከአካሉ ማስወጣትን ነው። በ1ቆሮ5:13 ላይም ተመሳሳዩ ቃል 'ይወገድ' ቀጥሏል። ሐዋሪያው የተጠቀመበትን ይህን ይወገድ የሚለውን ቃል በውስጥ እና በውጭ ከሚሉት ቃላት (1ቆሮ5:12) ጋር አብረን ስናየው የሚገልፀው የጌታን ራት ወይም ከቤተክርስትያኑ ሕንፃ ወይም ከጉባኤው ለማለት ሳይሆን (ይህ የማያምኑትንም ስለሚጨምር) ከቆሮንቶስ ቤተክርስትያን አባልነት ነው። ሐዋሪያው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልክት ይህንን ነው።

ሳውል «ሊተባበር» የሞከረው በትክክል ምንን ነበር? ከምዕመናኑ ጋር በቀላሉ ሊደባለቅ ነበርን የሞከረው? አልነበረም! ምክንያቱም በአጠቃላይ ከማኅበረ ምዕመኑ እንዲገለል በፍጹም አልተደረገም ነበረና። የአዲስ ኪዳን ጊዜ አማኞች በሕዝብ የአደባባይ ምስክርነታቸው ድፍረት አሳይተዋል ከዚህም ባሻገር የኢየሩሳሌሙ ስብሰባ ትልቅ መጠን ለሰው ሁሉ የአደባባዩን የስብከት አገልግሎት እንዲቀላቀለው ቀላል አድርጎለት ነበር። የቤተ ክርስትያን አባላት ሳውልን ፈርተውት ነበር የሚለው እውነት ስብሰባው ውስጥ እንዳይገኝ ከለከሉት አይደለም የሚለው።

ሳውልን ፈርተውት የነበረው የተጠጋጋ መንፈሳዊ ኅብረትና ክርስትያናዊ አገልግሎት አብሮ በማድረግ በኩል ነበር። እሱ ቢጥርም እንኳ በዚያ በጠለቀ ደረጃ እንዲደባለቃቸው አላደረጉትም። ሳውል ክርስቶስን አምነናል ካሉት ጋር በአባልነት ለመተባበር ይሞክር ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ይህንን ነገር ያረጋገጠው *ከደቀመዛምርቱ* ጋር ሊተባበር ይሞክር የነበረ መሆኑን በመጨመር ነው። ***ደቀመዛምርቱ*** የሚለውም ቃል በዚያን ጊዜ ለአመኑት ማህበረ-ሰብ (ኮሙኒቲ) ብቻ የተሰጠ ቃል ነበር። ሳውል ከደቀመዛምርቱ ጋር ሊተባበር ወይም ሊደባለቅ የቻለው በርናባስ ስለ እሱ ከተናገረ በኋላ ብቻ ነበር።

የመተባበር (መጣበቅ) ግስ

ይህም በዚህ እና በሌሎችም የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሰውን መተባበር ወይም መገናኘት የሚለውን ቃል ወደ ማጥናት ያመጣናል። መተባበር ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ግስ፣ ቃል በቃል ሲታይ መጣበቅ፣ መለበጥ፣ ወይም ሁለት ነገሮችን በሲሚንቶ እንደ ማያያዝ ማለት ነው። ይህ ቃል በግሪኩ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ሁልጊዜ የሚያመለክተው በጣም የተጠጋጋ መደጋገፍን ወይም አብሮ መተሳሰርን ነው።

አባካኙ ልጅ በጠፋበት በጉስቁልናው ጊዜ ሩቅ አገር ካሉ ሰዎች ጋር ሥራ ለመሥራት ራሱን አስጠጋ (አዳበለ ወይም አጣበቀ)። በዚህ ሥፍራ ቃሉ የሚገልፀው ጥገኝነትን፣ ለገንዘብ ብሎ ራሱን ለቀጣሪው የሰጠ ችግ ረኛ ሠራተኛን ነው።

በ1ቆሮ6:16 ላይም ይኸው ተመሳሳይ (የሚተባበር) የሚለው ቃል ለኃጢአተኞችም እንኳን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኅብረትን ለማሳየት ውሏል። እንዲሁም በ1ቆሮ6:17 ላይ ያው ቃል እንደገና የአውነተኛ ክርስትና ምልክት የሆነውን ሙሉ ለሙሉ መሰጠትን ለመግለጥ ጥቅም ላይ ውሏል ***«ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ነው።»***።

በሐዋ8:29 ለፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረው ወደ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሰረገላ ቀርቦ ራሱን እንዲያገናኝ ነው (ተመሳሳዩ የመጣበቅ ግስ) እርሱም አደረገው። በግብጥ እንዲሁም በጋራ ስምምነት ለዚያ ባለሥልጣን ቀረብ ብሎ መመስከሩን ቀጥሎ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተለውጦ ይጠመቅ ዘንድ አደረገው። የመጣበቅ ግስ ያለበትን ኃይለኛ ቋንቋ መንፈስ ቅዱስ እዚህ ቦታ ላይ የተጠቀመበት ይህ ሰው ጽድቅ ፈላጊ በመሆኑ በልቡ የእግዚአብሔር ጸጋ እየሠራ መሆኑን ምናልባት ለፊሊጶስ ለማመልከት

ይሆናል። ፊልጶስም በትዕግሥትና በጽናት መንፈሳዊ ሰንሰለቱ እስኪታይ ድረስ ተጣብቆ ወይም አብሮ መቆየት ነበረበት።

በአዲስ ኪዳን የመጣበቅ ወይም የመተባበር ግስ ይጠቅም የነበረው የተጠጋጋ፣ ልዩ ኃላፊነትን፣ ወይም መሰጠትን ለማሳየት ብቻ ነበር። እንዲሁም ቃሉ ባለበት በእያንዳንዱ አንቀፅ ውስጥ የሚታየው የጋራ ጥቅም ስላለበትና ሁለቱም ቡድን ስለሚስማሙበት ግንኙነት እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል።

ሌላው የመጣበቅ ግስ ጥቅም ላይ የዋለበት ምሳሌ የሚገኘው በሐዋ5:12-14 ነው። በሐናንያና በሰጲራ ላይ ከተፈረደው ፍርድ በኋላ ብዙ ሰዎች (ምናልባትም ግብዞችና እውነተኛ ክርስትያኖች ያልሆኑት ሰዎች) ከቤተክርስትያን ጋር ያላቸውን ግንኙነት አቋርጠዋል።

«በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር። ሁሉም በሰንደቅ ዕብ ሆነው በሰለሞን ደጅ መመላለሻ ነበረ። (አንዱ የመስበኪያ ቦታ ነበር) ***ከሌሎችም ሰንደቅ ሰንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር ሰው ነበረም ሕዝቡ ግን ያከብሯቸው ነበር። የሚያምኑትም ከፌት ይልቁ ብዜታ ይጨመሩበት ነበር ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበረ።»***

ክርስትያን አማኞች በሕዝቡ ዘንድ በጣም የተከበሩ የነበሩ ቢሆንም እንኳን ገና ብዙ ያልተቀላቀሏቸው ሰዎች ነበሩ። አሁንም ይህ አንቀፅ የሚናገረው ብዙው ሕዝብ በግልጥ አደባባይ (ሜዳ) ወደሚደረገው ስብከት እንደ ሰለሞን ደጅ መመላለሻ ዓይነት ቦታ ይሄድ እንደነበረ ነው። በእርግጥም በጉባኤው ውስጥ ሰው ጎድሎ አያውቅም ነበር።

ታዲያ በሐናንያና በሰጲራ ላይ ከሆነው ሁኔታ በኋላ ሕዝቡ ለመደባለቅ ምን አስፈራቸው? ብቸኛው መልስ የሚሆነው እውነታ - የቤተ ክርስትያን አባልነት - ነው። ምክንያቱም በጉባኤው ውስጥ በመገኘትና ከቤተ ክርስትያን ጋር በመጣበቅ መካከል ልዩነት ስለ ነበረው ነው!

እንደዚህ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎችን በጣም በተመለከትን ቁጥር በአዲስ ኪዳን ቤተክርስትያን ውስጥ የተወሰነ የአባልነት መዋቅር አልነበረም ብሎ ለመናገር እጅግ በጣም ያዳግታል።

በትክክል የተደራጀ መዋቅር

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከታቸው በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉት ቤተክርስትያን እውነተኛና በጋራ የተሰጡ አባላት አላት ብለን ስናስብ ብቻ ነው። ኤፌሶን5:21 የሚያዘን **«በእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሀት የተገዛችሁ ሁኑ»** በማለት ነው። ይህ ትእዛዝ ሕዝቡ ራሳቸውን እንደ አንድ ማኅበረ-ሰብ ማየት እንዳለባቸው የተሰጠ ትእዛዝ ነው። በመሆኑም ማኅበረ-ሰቡ ከግለሰብ በፊት ቀድሞ መምጣት አለበት። ወይም በጣም የተለየውን ገላትያ2:4 ላይ ያለውን ቃል እንመልከት:-

«ነገር ግን ባፈያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ሊየሱስ ያለንን ነጽነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር (ጠስውር፣ በግልፅ ገብቶ ለመሳተፍ አይፈቀድላቸውም ነበርና) ስለገቡ ስለሐሰተኛ ወንድሞች ነበረ።»

እዚህ የምናገኘው በሕዝብ ጉባኤ ከነበሩት ውስጥ ሁሉም

የማይካፈሉበት ስብሰባ ወይም ጉባኤ የነበረ መሆኑን ነው። በስብሰባው ለመካፈል ብቃት ያልነበረው በሚስጢር ነበር ሾልኮ የሚገባው። ይህ የአባላት ብቻ ስብሰባ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ምን ዓይነት ሌላ ስብሰባ ቢሆን ነው ሰዎች ሁሉ የማይሳተፉበት? የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስትያናት የተወሰነ አባልነት ያልነበራቸው ከሆነ ትርጉም ሊሰጡ የማይችሉ ሌሎች ተጨማሪ ብዙ ክፍሎች አሉ። ለመሆኑ ያለ ቤተ ክርስትያን አባልነት 1ጢሞ3:1 ላይ ያለውን ቃል ምን እናደርገዋለን? «**ማንም ሊደሰቆጸስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው።**»

የምን ኤጲስቆጶስ? ኤጲስቆጶስ ማለት የበላይ-ተመልካች ወይም የበላይ ተቆጣጣሪ ማለት ነው። የሚያመለክተውም እነዚያ የሚታዩት የበላይ-ተመልካቹን ሥልጣን መቀበል ያለባቸው መሆኑን ነው። (ይህም በዓለም እንዳለው በኃይል፣ ወይም በጌታ ሕዝብ መካከል እንዳለው፣ በፈቃደኝነት ማለት ነው)

የአዲስ ኪዳን የበላይ ተመልካች የቤተክርስትያን አገልጋይ ሆኖ ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስትያን ተጠያቂ ነን ብለው ራሳቸውን ለሰጡት አማኞች ኃላፊነት ያለበት ነው። እነሱም በአዲስ ኪዳን ያለውን የቤተ ክርስትያን አመራር ሥርዓት አምነው ተቀብለውት ነበር። ያን ጊዜ አባልነት ነበር እነሱም የዚያ አባልነት ክፍል ወይም አካል ነበሩ። ያለ እንደዚህ ዓይነት አባልነት የእረኝነትና የአስተዳደር አጠቃላይ መረዳት ውድቅ ይሆንና ቅዱስ ቃሉን መታዘዝ ሊኖር አይቻልም ነበር።

እንደዚሁም ከሽማግሌዎች የሥራ ዝርዝር አኳያ የአባልነትን አስፈላጊነት እናያለን። 1ጢሞ3:5- «**ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስትያን እንዴት ይጠብቃታል?**»።

አጥቢያ ቤተክርስትያን እንደቤተሰብ ናት። የአባት ሥልጣን ኃላፊነትና ተግባሮች ልክ እንደ ቤተክርስትያኑ የበላይ ተመልካች ነው። አንድ ሰው በቤት ውስጥ ሳይኖር የቤተሰብ አባል ሊሆን ይችላልን? አይችልም። የቤተሰብ አባልነት በቤት ውስጥ የተወሰነን ቦታ ያመለክታል። በ1ጢሞ5:17 ላይ የምናነበውም ቃል በተጨማሪ፡- «**በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች .... ይባረኩ**»።

አንድ ጊዜ እንደገና መጠየቅ ያለብን ጥያቄ የተወሰነና የተደራጀ አባልነት የሌለውን ቤተክርስትያን አንድ ሰው እንዴት ሊመራ ይችላል? የሚለውን ነው። አገርን ያለሕዝብ፣ ሠራዊትን ያለወታደር፣ ፋብሪካን ያለሠራተኛ ወይም ቤተሰብን ያለልጆች (ያለ ቤተሰብ አባላት) ማንም ሊመራ አይችልም።

ምሳሌዎቹ

ከነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተጨማሪ ቤተክርስትያንን ለመግለፅ የአዲስ ኪዳን ማብራሪያዎች ሆነው ከተሰጡት ታላላቅ ምሳሌዎች ውስጥ ሊካዱ የማይቻሉ የቤተክርስትያን አባልነት ተግባራት በሚገባ ተገልፀው ይገኛሉ። ማብራሪያዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የቤተመቅደስ ሕንፃ
2) አካል

3) ቤተሰብ
4) የወይን ግንድ
5) መንጋ
6) ሙሽራ
7) ካህናት ናቸው።

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምሳሌዎች አንድ አጥቢያ ቤተክርስትያንን በጣም በተለየ ሁኔታ ለመግለጥ ውለዋል። (የመጨረሻዎቹ አራት ምሳሌ ዎች ደግሞ በጣም የሰፉና በጠቅላላው አማኞችን ወይም *ዓለም አቀፍ የእግዚአብሔርን ቤተክርስትያን ይጨምራሉ።) የአጥቢያ ቤተክርስትያን መግለጫዎች የሆኑት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምሳሌዎች አማኞች ያለ ምንም ጥርጥር የቤተክርስትያን አባልነትን የመፈለግ ግዴታ እንዳለባቸው ያ ረጋግጣሉ። በተጨማሪም እነዚህ ምሳሌዎች ወይም ማብራሪያዎች በጣም ግልጥ አድርገው የሚያሳዩት እንደዚህ ዓይነት የቤተክርስትያን አባልነት በአጥቢያ ቤተክርስትያን ውስጥ ቃል-ኪዳንን ወይም መሰጠትን ያካተተ መሆኑን ነው። የአጥቢያ ቤተክርስትያኗን አስተምህሮ፣ ሥነ-ሥርዓትና አገልግሎት በትህትና መቀበልንም ይጨምራል።

የሕንፃው ምሳሌ

የሕንፃው ምሳሌ (በአብዛኛው ቤተመቅደሱ) በብዙ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ይገኛል። ኤፌ2:21 ላይ ያለው የሚለው፦ «***በእርሱም ሕንፃ ሁሉ ስቦተ ጋመመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስንዲሆን ያድጋል***»።

አባልነት ካልነበረ፣ እንዲሁም ሰው ሁሉ በዓይኑ ፊት መልካም መስሎ የሚታየውን የሚያደርግ ከነበረ፣ እያንዳንዱ ሰው በራሱና በግሉ ሊያደርገው በሚመኘው ዓይነት የክርስትያን ምስክርነትን ለመስጠት ቢወስን ኖሮ የእግዚአብሔር ሠራዊት ተፍረክርኮ በሥርዓተ-አልበኝነትና በግለሰባዊነት ይሞላ ነበር። እያንዳንዱን አማኝ በአካል በአዕምሮና በመንፈሳዊነት ያስዋበና የሠራ እግዚአብሔር፣ እንዲሁ ደግሞ ለእያንዳንዱ አባል ቦታን መድቧል። በሕንፃ ውስጥ ድንጋዮች፣ ማዕዘኖች፣ ጣውላዎች፣ መቃኖችና ሌሎችም በየራሳቸው ትክክለኛ ቦታ ሳይነቃነቁና በጽናት እንደተ ቀመጡ ጌታም ሕዝቡን ወደ አባልነት የጠራው አንድ ላይ ሆነው አመራርንና የጋራ ሥርዓትን እንዲቀበሉና በመንፈስ ቅዱስ አመራር ወደፊት እንዲገሰግሱ ነው።

በጌታ እንደተመደበውና እንደታሰበው ስለ አጥቢያ ቤተክርስትያን አስደናቂ የሆነ ሥነ-ሥርዓት አለ። በተጨማሪም 1ጢሞ3:15 አባልነትን በጣም ኃይለኛ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፦ «***በስንዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር ስንዴት ስንደሚገባ ታውቅ ዘንድ ስጽፍልህለሁ ቤቱም የስሙነት ዓምድና መሠረት የሕያው ስንዚአብሔር ቤተክርስትያን ነው***»።

---

*ዓለም አቀፍ ቤተክርስትያን፦ የማትታየዋንና ከሰው ዘር ሁሉና ከየትኛውም የዕድሜ ክልል እንዲሁም ዘመን ያሉትን አማኞችን ሁሉ ያቀፈችውን [Universal Church] ያመለክታል።

አንድ ጊዜ እንደገና አጥቢያ ቤተክርስትያን የተነሣፀረችው ከሕንፃ ጋር ነው፣ ያም መሠረትና አብሮ የሚደግፈው ማዕዘን ያላት ሆና ነው። እንደ ጠንካራ የቤተመቅደስ ግንብ አባላቱ የሚደግፉትና የሚወክሉት ራሱን *እውነትን* ነው። ባሕሪያቸውም ለእንደዚህ ዓይነት ምሳሌ ምቹ (የተስማማ) መሆን አለበት። ይህም እያንዳንዱ አባል ጠቃሚ የሆነ የሕንፃው ሸክም ተሸካሚ ክፍል፣ እንዲሁም የታቀደውና የተቀናጀው መዋቅር ክፍል አካል ነው ማለት ነው። ማንኛውም ክርስትያን ከዚህ ወጭ የሆነ አይደለም። ክርስትያን ሆኖ የቤተክርስትያን አባል ያልሆነ ሰው ሊኖር አይችልም። የትኛውም የሕንፃው ግድግዳ ወይም የመስኮት ፍሬም እየተላቀቀ ወደ ውስጥ ወይም ወደ ውጭ ማለት እንደሌለበት ሁሉ ከአባልነት መሰጠት ውጭ የሆነ የክርስትያን ነጻነት፣ ከክርስትና የመሰጠት ሕይወት ጋር የተቃረነ ነው። ስለዚህ በዚህ የሕንፃ ምሳሌ ውስጥ የአባልነት አስፈላጊነት ተገቢ የሆነ ትምህርት ተሰጥቶበታል።

የአካል ምሳሌ

የአካሉ ምሳሌም እንደዚሁ በብዙ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ይገኛ ል። በ1ቆሮ12፡12 ላይ *«ሰላልም ሰንድ ስንደሆነ ብዙም ብልቶች ስንዳሉት ነገር ግን ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ ሰንድ ሰላል ስንደሆኑ ክርስቶስ ደግሞ ስንዲሁ ነው።»* ተ ብሎ እንደተገለጠው አጥቢያ ቤተክርስትያን እዚህ ክፍል ውስጥ የምትታየው ከሰው አካል ጋር በጣም ተመሳሳይ ሆና ነው። በሌላ አነጋገር አካል አንድ እና የተለያዩ የአካል ክፍሎች በግድ በተፈጥሮ በትክክል የተ ጣበቁበት ነው። ሊገነጣጠሉ አይችሉም፣ ወይም መያያዛቸው አልፎ-አልፎ የሆነ አይደለም። የአካል ክፍሎች በተፈጥሮ የተያያዙና በሙሉ ሰውነት ላይ የተደጋገፉ ናቸው። በሁሉም ክፍሎች መካከል ታላቅ የሆነ መቀናጀትና መስማማት አለ።

ምሳሌው አስገራሚ ነው በመሆኑም በአባላት መካከል መተባበርና ሥርዓትን የያዘውን የአጥቢያ ቤተክርስትያንን የአባልነት አስፈላጊነት ምንም በማያነታርክ መልኩ መሥርቶታል።

የተማርነው ነገር አንድ ማኅበረ ምዕመን አንድ ሰባኪን ሊሰሙ ከተ ሰበሰቡ ብዙ ሰዎች ያለፈ ወይም የበለጠ መሆኑን ነው። በቤተክርስትያን አባልነት ውስጥ የሚታየው አባላቱ ሁሉ በጣም ጠቃሚ ሥራ ያላቸውና ሙሉው ቤተክርስትያን የተመሰረተው በያንዳንዱና በመላው አባላት ላይ ሆኖ ነው። በአባልነት ውስጥ መተባበር ሥርዓትና የጋራ አመራር አለበት። ኤፌ4፡15 ይህንን ምሳሌ እንደሚከተለው ያብራራዋል፡- *«ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደገ ከእርሱም የተነሳ ሰላል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በዕስ እንደሚወራ በተሰመጠት በጅማት ሁሉ እየተ ጋመመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር ሰማነፅ ሰላሱን ያሳድጋል»*

እግዚአብሔር በቤተክርስትያን ውስጥ እኛን አንድ ላይ ያያያዘበት አንዱ ምክንያት እያንዳንዱ የሱ ሕዝብ ለአካሉ ማደግና ለእውነተኛ የወንጌል ስርጭት ተሳታፊ መሆኑ ጠቃሚ ስለሆነ ነው። እጅ ወይም አንድ የሰውነት ክፍል ከሰውነት ተገንጥሎ ለብቻው በአንድ በሌላ ቦታ ሊቀመጥ ከቶ ይችላልን? እንደዚሁም ደግሞ አንድ ክርስትያን የቤተክርስትያን አባል

ላለመሆን ሊመርጥ ይችላል ተብሎ ሊታሰብ ይቻላልን? የቤተክርስትያንስ አባል መሆን ለማይፈልግ ሰው በአዲስ ኪዳን ላይ የሚረዳ ደንብ ወይም አሳብ ይኖራልን?

ለዚህ ጥያቄ ብቸኛው መልስ የሚሆነው የሚከተለው ነው፡ - ይህም አንድ ሰው በአንድ በተወሰነ ምክንያት ከቤተክርስትያን፣ በአርምተ ቤተ ክርስትያን (ዲሲፕሊን) ከተገለለ ብቻ ነው። ከዚህ በቀር በአዲስ ኪዳን አንድ አማኝ የቤተክርስትያን አባል የማይሆንበት ሌላ ምንም ምክንያት የለም።

የቤተሰብ ምሳሌ

አንድ ሰው **«እኔ የቤተክርስትያን አባል ለመሆን በእምነት በጣም ገና ነኝ ብዬ አስባለሁ»** ይላል ብለን ብናስብ በፍጥነት መመልከት ያለብን የመጽሐፍ ቅዱስን የቤተሰብ ምሳሌ ነው (1ጢሞ3፡5)። በቤተሰብ በተመሰለችው በቤተክርስትያን ውስጥ አባል ላለመሆን ማንኛውም አማኝ በጣም ገና አይደለም። አንድ ትንሽ ሕፃንን የቤተሰብ አባል ተብሎ ሊቆጠር በጣም ገና በመሆኑ ከበር ውጭ ነው መተው ያለበት ብሎ ማንም አሳብ ሊያቀርብ አይችልም። እንዲያውም ሕፃኑ ራሱን ያልቻለና ገና ደካማ ከመሆኑ የተነሣ ከቤተሰቡ ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግለት ይገባዋል። በእርግጥ ቤተሰብ የተመሠረተው በመተባበር፣ በሥርዓት፣ በቤት ኃላፊና በጋራ ዓላማ ነው። እኛም እንደ ቤተሰብ በደም የተሳሰርን ነን። እኛ እንደ ቤተሰብ አብረን የተደራጀን ነን። ስለዚህም አንዳችን ለአንዳችን ጉዳይ የማያቋርጥ ትኩረት እንሰጣለን። ምክንያቱም አንድ ስም የምንካፈልና በአንድ የቤተሰብ አንድነት ውስጥ ያለን ነንና።

በመሆኑ ዳግም እንደተወለዱ አማኞች እኛ ራሳችንን ከራሱ ሕዝብ ጋር በአባልነት እንድናጣብቅ በአዳኛችን ታዘናል። ልንደባለቅባት የወሰንነውም ቤተክርስትያን በመንፈስ ቅዱስ ለተሰጠው ስሕተት ለሌለበት ለእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ የተሰጠችና ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ገጾች ላይ በአጭሩ እንደቀረበው መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የክርስቶስን ቤተክርስትያን መርሆ ለማሟላት የምትጥር መሆን አለባት።

የአጥቢያ ቤተክርስትያን ባሕርያት

የክርስቶስን አጥቢያ ቤተክርስትያናት ባሕርይ የሚወስኑ አራት መርሆዎች እንዳሉ አዲስ ኪዳን ያስተምራል። እነዚህም አራቱ መርሆዎች፡-

1) የእያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስትያን ራስና ጌታ ክርስቶስ ነው። እያንዳንዷ ሙሉ አጥቢያ ቤተክርስትያን ሙሉ ለሙሉ ራሷን የቻለች፣ ራሷን በራሷ የምታስተዳድር እና በሌላ በማንም ቤተክርስትያን የሥልጣን ተዋረድ ወይም ቤተ-እምነታዊ ሥልጣን ሥር አይደለችም።
2) ለቤተክርስትያን አባልነት ተቀባይነት ያላቸው ዳግም የተወለዱ አማኞች ብቻ ናቸው። ይህም ዳግም የተወለዱ አባልነት መርሆ ነው።
3) እያንዳንዱ የቤተክርስትያን አባል ለአጥቢያ ቤተክርስትያን ጎብረትና አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ የተሰጠ መሆን አለበት።
4) ለጌታ እየታዘዘች የምትኖር እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስትያን እንደ አንድ አስፈላጊ መንፈሳዊ ሕይወት የማደግ ባሕርይ ይኖራታል።

1. ራሷን የቻለች

የመጀመሪያው ታላቅ መርሆ እያንዳንዷ ቤተክርስትያን ራሷን የቻለች ወይም ጥገኛ ያልሆነች መሆን አለባት የሚለው ነው። የሌላ የማንኛውም ቤተክርስትያን የበላይ ተመልካችነት፣ የአገልግሎት ፈቃድ ሰጪነት፣ ከማንኛውም ቤተክርስትያናዊ የሥልጣን ተዋረድ አገዛዝ ወይም ርዳታ አያስፈልጋትም። እያንዳንዷ ቤተክርስትያን ጌታን እስከታዘዘች ድረስ የምትሆነው በክርስቶስ የቀጥታ አስተዳዳሪነት ምሪትና በረከት ሥር ውስጥ ነው።

የአዲስ ኪዳን መልእክቶች የተጻፉት ለአጥቢያ ቤተክርስትያናት (ወይም ለአጥቢያ ቤተክርስትያናት መጋቢዎች ወይም የቢሮ ኃላፊዎች) ነው። መልእክቶቹም የተጻፉት እነዚያ ቤተክርስትያናት ራሳቸውን የቻሉ የነበሩና በየትኛውም ማዕከላዊ ድርጅት ወይም ሥልጣን ሥር ያልነበሩ መሆናቸውን እንዳንጠራጠር በሚያደርግ መልኩ ነው። እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስትያንም በግሏ ተጠሪነቷ ለጌታ ነበረ። እያንዳንዷ እንደ አጥቢያ ቤተ ክርስትያን የራሷ «ሙሉ ሥልጣን» ነበራት።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የትኛውንም ዓይነት የቤተክርስትያኖች ድርጅት አልመሠረተም ነበር። ራዕይ2:1 ለዚህ እውነት ቁልፍ ጥቅስ ይሰጠናል፡- «***በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተክርስትያን መልዕክት (ምናልባትም አገልጋዩ) እንዲህ ብለህ ጻፍ፣ በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል፡-***»

ቤተክርስትያናቱ በቀጥታ በስም የተጠሩት በመካከላቸው በሚመላለሰው በራሱ በጌታ ነው። በራዕይ1:20 ላይ እንደተነገረን መቅረዞቹ ቤተክርስትያናቱ ናቸው። ከእያንዳንዷም ቤተክርስትያን ጋር ለመንቀፍ፣ ለማበረታታት ወይም ለመገሠጽ በቀጥታ ሲሠራ የሚታየው ራሱ ጌታ ነው። ጳጳስ፣ ሊቀጳጳስ፣ የአጥቢያ ተቆጣጣሪ፣ ሲኖዶስ፣ ወይም እንዲህ ዓይነት ጣልቃ ገብነት በፍጹም አልተጠቀሰም። እያንዳንዷን ጎብረት

ለመግዛት ለማበረታታትና ለመቆጣጠር ጌታ የሆነው ራሱ ክርስቶስ ነው።

ለዚህ እውነት በጣም ተግባራዊ የሆነ ማረጋገጫን ለማግኘት ከፈለግን ሐዋ13:1-2 ላይ ያለውን መመልከት እንችላለን:- «***በዚያንጊያም ባሰችው ቤተክርስትያን ነቢያትና መምህራን ነበረ ..... ስነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ: - በርናባስንና ሳውሎን ስጠራቸው ሥራ ስየሰጣቸው ነው***»።

በዚያን ጊዜ ብዙዎቹ ሐዋርያት ይኖሩ የነበረው በኢየሩሳሌም ካለችው ቤተክርስትያን ጋር ነበር። እነዚህ ቁጥሮች ላይ ያለው ቃል የሚያሳየን መንፈስ ቅዱስ ወደ አንያኪያ ቤተክርስትያን የሄደው በቀጥታ እንጂ በኢየሩሳሌም ቤተክርስትያን በኩል አለመሆኑን ነው።

እግዚአብሔር በአንድ አጥቢያ ቤተክርስትያን ውስጥ ያሉትን መሪ ዎች በማንቀሳቀስና ሥልጣን በመስጠት፣ ሰዎችን ለአገልግሎት ሥራ እንዲለዩና እንዲመድቡ በቀጥታ ይሠራባቸዋል። በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተክርስትያን ጥላ ውስጥ የምናየው ቤተክርስትያን ራሷን የቻለች የተለየች ሆና በጌታ ስትመራና ስትገዛ ነው። በዚያ ቦታ ምንም ዓይነት የሐዋርያት የሥልጣን ተዋረድ አልነበረም።

አጥቢያ ቤተክርስትያን በቀጥታ የክርስቶስ ንብረትና ደስታ የመሆኗ ጠቀሜታ የሚታየው በአዲስ ኪዳን «ቤተ-ክርስትያን» የሚለው ቃል ምን ያህል ጊዜ የመጠቀሱን እውነታ ስናስተውል ጭምር ነው።

«ቤተክርስትያን» ቃሉ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ቤተ-ክርስትያን» ተብሎ የተተረጎመው ቃል የመጣው «ኤክሌሽያ» ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ትክክለኛ ትርጉሙም «ተጠርተው የወጡ»፣ «ወጥተው የታደሙ»፣ ወይም «የተሰበሰቡ--ጉባኤ» ማለት ነው።

ይህ «ኤክሌሽያ» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 114 ጊዜ ተጠቅሷል። ይህም ቁጥር በጣም ጠቃሚ የሚሆነው ቃሉ በፍጹም የማይጠቅሰውን በምናውቅበት ጊዜ ነው። በእነዚህ 114 ማስረጃዎች ሁሉ ላይ «ኤክሌሽያ» የሚለው ቃል የተተረጎመው ቤተክርስትያን በሚለው ሲሆን ፈጽሞ «ሕንፃን» ለመግለጥ አላገለገለም። አንድም ጊዜ አገር አቀፍ ቤተ ክርስትያንን ለመግለጥ አላገለገለም። አንድም ጊዜ ቤተ-እምነትን ወይም የቤተክርስትያናት ቡድንን ለመግለጥ አላገለገለም። አንዱም እንኳ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አገር አቀፍ ወይም ዲኖሚኔሽናል ቡድኖች «ቤተክርስትያን» ተብለው በፍጹም አልተጠቀሱም። ቤተክርስትያን (ኤክሌሽያ) የሚለው ቃል ከተጠቀሰበት ከአምስቱ ቦታ በአራቱ ላይ ያገለገለው በአንድ ቦታ ወይም ከተማ «ወጥተው የተሰበሰቡ» የክርስትያን ማኅበረ-ሰብን ስብሰባ ለመግለጥ ነው። ከተጠቀሰበት ከአምስቱ በአንዱ ላይ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ምርጥ ሕዝብ በጠቅላላው ነው፣ ማለትም ከሁሉም የዕድሜ ክልልና ከሁሉም የሰው ዘር አማኞች የተሠራችውን «የማትታየዋን» ዓለም አቀፍ ቤተክርስትያንን ለመግለጥ ነው። ነገር ግን ቤተክርስትያን የሚለው ቃል በአብዛኛው የሚያሳየው የተወሰነች አጥቢያ ቤተክርስትያንን ነው (ለምሳሌ: - «***በቤትህ ባለችው ቤተክርስትያን ሰላምታ ስቅርብልኝ***») (ቆላ4:15 ፊሊሞና2)።

ስለዚህም ይህን «ቤተክርስትያን» የሚለውን ቃል ማወቅ በአዲስ ኪዳን የነበሩትን የእያንዳንዷን አጥቢያ ቤተክርስትያን በጣም ትልቅ ጥቅም እንድናይ ይጠቅመናል። በአዲስ ኪዳን መልእክቶች በቀጥታ ትምህርት የተሰጣቸውና የታዘዙት አጥቢያ ቤተክርስትያንና አባላቶቿ ናቸው።

የምሳሌዎቹ ዳግመኛ ጠቀሜታ

በመጨረሻም የቤተክርስትያንን ምሳሌዎች እንደገና በምንመለከትበት ጊዜ እያንዳንዷ ቤተክርስትያን በቀጥታ ተጠሪነትዋ ለእግዚአብሔር ሊሆን እንደሚገባው ተጨማሪ ማስረጃዎችን እናያለን። ለአጥቢያ ቤተክርስትያን የሚያገለግሉት ዋነኞቹ የቤተክርስትያን ምሳሌዎች አካል፣ ሕንፃና ቤተሰብ ናቸው።

እያንዳንዱ አካል ከሌላው የተለየና የሚመራውም በራሱ እራስ ነው። የአካል እራስ ክርስቶስ ነው (ኤፌ.4:15 ተመልከት)። አካል የወከለው አጥቢያ ቤተክርስትያንን ነው። ስለዚህ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስትያን በቀጥታ በክርስቶስ ሥር ናት። ይህ የቤተክርስትያን ምሳሌ ለሰው-ሠራሽ የሥልጣን ተዋረድ ወይም የአገር አቀፍ ቤተክርስትያን ቦታ የለውም።

የቤተ መቅደሱ ሕንፃ ሌላው የአጥቢያ ቤተክርስትያን ምሳሌ ነው (1ቆሮ3:9-17)። የዚች አጥቢያ ቤተክርስትያን መሠረት ክርስቶስ ነው (ቁ 11)። በተጨማሪም እሱ የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ነው (ኤፌ.2:22)። በሌላ አነጋገር እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስትያን የተመሠረተችው በክርስቶስ ላይ ነው።

ቤተሰብም ሌላው የአጥቢያ ቤተክርስትያን መግለጫ ነው፣ እኛም የሕያው እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን። እያንዳንዱም ቤተሰብ ራሱን የቻለ ክፍል «አሀድ» ሆኖ ከአባቱ ጋር በጣም የተጠጋጋ፣ የተቀራረበ፣ ልባዊ የሆነ የፍቅር ግንኙነት ያለው ሆኖ ይናራል። ልክ በዚህ ዓይነት ስሜት ነው እያንዳንዷ ቤተክርስትያን የጌታን ቀጥተኛ የአባትነት እንክብካቤ ሐሴት የምታደርገው። እያንዳንዷ ቤተክርስትያን ራሷን የቻለችና ከጌታ ጋር በአስደናቂ ቀጥታ ግንኙነት ላይ የተመሠረተች ናት። እንደገና አንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ጥቅስ ማስታወስ ባንችል የእግዚአብሔር ቃል የሰጠንን ምሳሌዎቹን ማስታወስ እንችላለን ።

2. የተለወጡ አባላት ብቻ

የቤተክርስትያናትን ባሕርይ ከሚወስኑት መካከል ሁለተኛው መርሆ አባልነት ሁልጊዜ መሆን ያለበት በእውነት ወደ ጌታ መጥተው ለተለወጡና የተረጋገጠ እምነት ላላቸው ሰዎች ብቻ ነው የሚለው ነው። አባልነት ዳግም ለተወለዱ ሰዎች ብቻ ነው የሚለው ሕግ የተወሰደው ከአዲስ ኪዳን መልእክቶች ላይ ነው። ሐዋርያው ሮም ላለችው ቤተክርስትያን ሲጽፍ እንዲህ አለ:- «***በእግዚአብሔር የተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላሳችሁ ሁሉ .... ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን*** » (ሮሜ1:7)።

በቆሮንቶስም ላለችው ቤተክርስትያን ሐዋርያው የተናገረው ያንኑ ነው አሁንም እንደገና የነሱ አባልነት ሙሉ ለሙሉ የተሠራው ወይም የተመሠረተው ጌታን በእውነተኛ መንፈሳዊ ልምድ ባገኙት ላይ ነው።

«በቆሮንቶስ ላሰች ለእግዚአብሔር ቤተክርስተያን በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት» (1ቆሮ1:2)::

የቆላስያስ መልእክትም የመክፈቻ ሰላምታ እንዲሁ ቤተክርስትያኒቱ የተለወጡ አባላት ያሏት ለመሆኑ ጥርጥር ውስጥ አይጥለንም:- *«በቆላስያስ ለሚኖሩ ቅዱሳንና በክርስቶስ ለታመኑት ወንድሞች»* (ቆላ1:2)::

እያንዳንዱም መልእክት ተመሳሳይ ሰላምታ አለው:: ይህንንም ጠቃሚ መርሆ የሚያረጋግጡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚኖሩን ሲሆን አንዱን ከሌላው መምረጡም አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን የመጨረሻ ማረጋገጫ ከሐዋርያት ሥራ ላይ ሊወሰድ ይቻላል ይህም እንደሚከተለው ተመዝግቧል:- *«ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በአንድነት ላይ* (በኢየሩሳሌም) *ይጨምር ነበር »* (ሐዋ2:47)::

ለዚህ ትምህርት ያለው ብቸኛ ተቃውሞ ድብልቅ የቤተክርስትያን አባልነትን ለመደገፍ በሚመኙ ሰዎች ነው (የወንጌላውያንን የእምነት ውሳኔን ያላደረጉ ወይም ግልጥ የሆነ የመለወጥ ልምድ የሌላቸውን ጨምሮ አባል የሚያደርጉትን ማለት ነው):: እነሱም የሚናገሩት የቤተክርስትያንን ንጽሕና በፍጹም ማምጣት አይቻልም፣ ስለዚህ ይህንን ንጽሕና ለማምጣት መሞከር ጅልነት ነው የሚል ሃሳብን ነው:: (ተመሳሳዩ እንዲያውም ደካማው ክርክራቸው ለቅድስና ሕይወት በመጣር ሥራ ላይ ነው)::

የድብልቅ አባልነትን አሳብ በመደገፍ በኩል ሊጠቀስ የሚችለው ብቸኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከማቲ13:24 የሚጀምረው የስንዴና የእንክርዳዱ ምሳሌ ብቻ ነው:: በነሱም አመለካከት ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ነገር አገልጋዮቹ እንክርዳዱን እንዳይነቅሉ ታዘዋል በሚለው አሳብ ላይ ነው:: ምክንያቱም ስንዴው አብሮ ይነቀላልና! ባለቤቱም እንዲህ አለ:- *«ተዉአቸው ስለስ መከር ጊዜ ሲደርሰው እሸዳን በመከር ጊዜም ሰሚጸዳችን ስንክርዳዱን ስስቀድማችሁ ሀቀሙ በስሳተም ስማቃጠል በየነዱው ስስረ ሰንዲሙን ግን በንተራዩ ክተቱ ስባስሙ»* ይላል::

ነገር ግን እዚህ ጋ የሚነሳው ጥያቄ:- በዚህ ምሳሌ ውስጥ የእርሻው ቦታ የሚያመለክተው ምንን ነው? የሚለው ነው:: የቤተክርስትያን ድብልቅ አባልነትን የሚደግፉት የሚሉት የእርሻው ቦታ የሚያመለክተው «ቤተ ክርስትያንን» ነው:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ራሱ የተናገረው *«እርሻው ዓለም ነው»* (ቁ 38) በማለት ነው:: በመሆኑም ይህ ምሳሌ እንክርዳድና ስንዴ አብ ረው በቤተክርስትያን ውስጥ እንዲያድጉ አያስተምርም:: እርሻው ሙሉ በሙሉ የዓለም ምሳሌ ነው:: በመሆኑም የቤተክርስትያን አባልነት ዳግም ለተወለዱ ብቻ ነው በማለት ከጸናው እንዲሁም ይህንን በግልጥ ከሚያስተምረው ከእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ጋር ይሄኛውም የእንክርዳዱና የስንዴ ምሳሌ ፈጽሞ አይቃረንም::

ሕይወት በምሳሌዎቹ ውስጥ

በዚህ መርሆ ላይ ያለውን ማንኛውንም የመጨረሻ ጥርጥር ለማጥፋት አንድ ጊዜ እነዚያን ታላላቅ የቤተክርስትያን ምሳሌዎችን ልናስብ ብቻ ይገባናል:: ስለዚህም አንድ ጊዜ እንደገና ከሁኔታው ጋር የሚስማሙትን

ማስረጃዎች ብቻ እንመለከታለን::

በመጀመሪያ የአካልን ምሳሌ አስቡ:: እያንዳንዱ እጅና እግር እንዲሁም የአካል ክፍል ሕይወት ያለው ነው:: ሰውነት የሞተ የአካል ክፍልን ወይም የሞተ እጅና እግርን በርግጥ አይቀበልም:: ስለዚህ ቤተ ክርስትያን ዳግም የተወለዱትንና ያልተወለዱትን አደባልቃ የያዘች ናት የሚለው አሳብ ከአካሉ ምሳሌ ጋር ፈጽሞ አይሄድም::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመጀመሪያ እይታ ሲታይ መንፈሳዊ «ሙት» አባላትን የሚፈቅድ የሚመስለው የሕንፃው ምሳሌ ነው:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ምሳሌ እስከ መቀየር ድረስ ይሄድና፣ የቤተክርስትያን አባላት ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው በማለት በጣም ያጠናክረዋል (1ጴጥ2:-5):: ስለዚህም በቤተመቅደሱ ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወት የሌላቸው ድንጋዮች የሉም ማለት ነው::

የቤተሰቡም ምሳሌ ሙት አባላትን እንደማያካትት በጣም ግልጽ የሆነ ነገር ነው:: በቤተሰብ ውስጥ ያሉት ከቤተሰቡ ራስ ከጌታ ጋር ጎብረት ያላቸው ሕያዋን አባላት ብቻ ናቸው:: ሌሎቹም የቤተክርስትያን ምሳሌዎች በሙሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚያሰሙት ዳግም ለተወለደ የቤተ ክርስትያን አባልነት ነው:: በወይኑ ግንድና በቅርንጫፎቹም ምሳሌ ላይ ያለው ፍጹም ግልጥ የሆነ ትምህርት የግንዱ ባሕርይ ለዳኑ ወይም ዳግም ለተወለዱ ለቅርንጫፎቹ ሁሉ መሆን እንዳለበት ነው:: በመሆኑም በወይኑ ግንድ ላይ የቀርቀሀ ወይም የቀጋ ዛፍ መሆን አይቻልም:: ምሳሌው የሚጠይቀው የዛፉ ባሕርይ ሕይወት ካላቸው ቅርንጫፎች ጋር ፍጹም ተ መሳሳይ መሆን አለበት ነው::

ስለዚህ ዳግም የተወለደው አማኝ ከምን ዓይነት ቤተክርስትያን ጋር ነው መደባለቅ ያለበት? መልሱም የሚሆነው በግልጥ በምትታየውና የዳኑ ሕዝቦች ካሉባት ቤተክርስትያን ጋር ነው:: ጌታ ያዘዘው የአጥቢያ ቤተ ክርስትያን አባልነትን ሊገነቡ የሚችሉት በእውነት የተለወጡ አባላት ብቻ መሆናቸውን ነው::

3. ሙሉ በሙሉ የተሰጡ

የእያንዳንዷን የክርስቶስን አጥቢያ ቤተክርስትያን ባሕርይ ሊገዛ የሚገባው ሦስተኛው አስፈላጊ መርሆ፣ አባላት አንድ ልብ ያላቸው፣ በአስተ ምህሮ የተጠጋጉ፣ ለጌታ አብረው በቅናት የሚሠሩ፣ እርስ በእርስ ባላቸው ፍቅር አብረው ለማደግ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው:: በሌላ አነጋገር ለጎብ ረትና ለአገልግሎት ሙሉ ለሙሉ የመሰጠት መርሆ ማለት ነው::

ሆኖም በራሳቸው አሳብ የሚመሩ አንዳንድ አማኞች የሚከተለውን እንዲህ በማለት:- **«የአጥቢያ ቤተክርስትያን አባል ከሌላው ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የመፍጠሩ ምክንያት አይታየኝም በርግጥ አንድ ሰው አምልኮ ሊካፈል አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚችለው ጎብረት መፍጠር አለበት ነገር ግን አንዳንድ ነገሮችን ራሱ ለራሱ መጠበቅ አለበት»** ሊሉ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ ቤተክርስትያን እኮ ፑልፒትና ምዕመን ብቻ ማለት በፍጹም አልነበ ረችም:: ነገር ግን ንቁ ሕይወት ያለው አባልነት ያለባት እያንዳንዱም አባል በሮሜ 12:1 ላይ ልናይ እንደምንችለው ሙሉ ለሙሉ የተሳተፈባት ነበረች::

«ስንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን ስግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በስግዚአብሔር ርኅራኄ አስምናችኋለሁ አርሱም ሰአስምር የሚመች ስገሳችሁ ነው።»

ሮሜ አስራ ሁለት ምዕራፍ በሙሉ ግልጥ እንደሚያደርገው ይህ ቁጥር ወይም ቁጥር አንድ የቤተክርስትያን አባልነት አነስተኛው መለኪያ መሆኑን ነው። በጣም ጠቃሚው ቁጥር ደግሞ የሚገኘው በቆላስ2:5 ላይ ነው። በዚህም ቁጥር ላይ ሐዋርያው የተናገረው፡- **«ሥጋ ምንም ስንኳ ብርቀ በመንፈስ ከስናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የስምነታችሁን ፀናት ስያየሁ ደስ ይስኛል።»** በማለት ነው።

በዚህ ክፍል ውስጥ «ሥርዓት» ተብሎ የተተረጎመው ቃል ሥርዓት ወይም ሥነ-ሥርዓት ከሚለው ቃል የላቀ ትርጉም ያለው ነው። የቃሉም ትርጉም ቅደም ተከተል ወይም (በጦር ሠራዊት እንዳለው) የሥልጣን ተዋ ረድ ወይም በክብር የሚሰጥ አመዳደብ ማለት ነው።

ቃሉ የሚያሳየው በቆላስያስ ቤተክርስትያን አገልግሎት ውስጥ እያንዳንዱ አባል በሚያምር ሁኔታ የተወሰነ የአገልግሎት ሥፍራ ቦታ በሥነ-ሥርዓት የነበረው መሆኑን ነው። ቤተክርስትያኗም እያንዳንዱ ሰው በአንድ የጦርነት ዕቅድ ውስጥ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ የያዘንና ለጦርነት ዝግጁ የሆነን የጌታ ሠራዊት ወይም የጦር ባታሊዮን ትመስል ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ ያስታወሰው ነገር የቆላስያስ ቤተክርስትያንን አባላት ሙሉ ለሙሉ ለጌታ ሥራ መሰጠትን ነበር። በመሆኑም ወንዶች፣ ሴቶች እና ወጣቶች ሁሉ ለጎብረቱ ሥራ ይተጉ ነበር። መንፈሳዊ ስጦታ ዎችም ሁሉ በጋራ አመራር ሥር በሚገባ በአገልግሎት ላይ ውለው ነበር።

ይህ ሙሉ ለሙሉ ማለትም በሙሉ ልብ ለአጥቢያ ቤተክርስትያን የመሰጠት መርሆ የተለየ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ነውን? በሌላ አንፃር ወደ ቤተክርስትያን ምሳሌዎቹ እንደገና ብንመለስ የምናገኘው ነገር ቢኖር ሁሉም ምሳሌዎች ይህ ሙሉ ለሙሉ የመሰጠት መርሆ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ነው።

አካሉን ብንወስድ፣ ምን ዓይነት አንድነትና መዋሐድ ነው በአካሉ ውስጥ ያለው? አካል በከፍተኛ ደረጃ የተቀናበረና የተደራጀ ተፈጥሮ ነው። ዓይንና እጅ አብረው ነው የሚሠሩት። ይህ የትልቅ አንድነትና አንዱ በሌ ላው ላይ ጥገኛ መሆኑን በትክክል የሚያሳይ ምሳሌ ነው (1ቆሮ12:13-27)።

በሕንጻው ምሳሌ ውስጥ የቤተመቅደሱ ድንጋዮች አብረው በመሰካካት መያያዝ ያለባቸው መሆኑ ይህንን ትምህርት እንደገና ይደግመዋል። እያንዳንዱ በጥብቅ መያያዝ አለባቸው በመሆኑም ቅስቱና ጣሪ ያው ሕንፃውን በሚገባ ይደግፋሉ። እንደገና ይህ የአካሉ ሁሉ የተውጣጣ የጋራ ጥረትና ያለው (ሪሶርስ) ሁሉ በአገልግሎት ላይ የመዋሉ ምሳሌ ነው።

የወይኑ ግንድም ምሳሌ የሚያሳየው ለአዲስ ኪዳን ቤተክርስትያን የታሰበውን ባሕርይ ነው። በዮሐንስ15 ላይ የተማርነው የሞቱትና ንቁ የሆነና ሕይወት ያለው ተሳትፎ የሌላቸው ቅርንጫፎች መኖር አሳብ ለጌታ አስከፊ መሆናቸውን ነው። የቤተሰቡም ምሳሌ የሚሰጠው ማብራሪያ አጥቢያ ቤተክርስትያን በጋራ መተሳሰብ የቤት ውስጥ ሥራን ተከፋፍለው አብረው ለመኖር ጥረት የሚያደርጉ የቤተሰብ አባላትን ነው የምትመስለው።

የቤተክርስትያን ምሳሌዎቹ አንድ ላይ በሙሉ አምልኮ፣ በጎብ ረታችን ሥራ ወጤት፣ እርስ በእርስ በጣም የተቀራረብን እንድንሆን ከፍተኛ ኃላፊነት ይጥሉብናል።

በመሆኑም ከዚህ መራቅ፣ መገለል፣ ቁጥብ መሆን፣ መስነፍ፣ ግዴለሽነት፣ ንዝህላልነት፣ ትልቅ ስሕተትና በዚህ ጉዳይ ላይ ጌታ ያስተማ ረውን በፍቃደኝነት መቃወምና መንቀፍ ማለት ነው።

4. ሕይወት ያለው እድገት

የክርስቶስ ቤተክርስትያንን የሚገዛው አራተኛው ጠቃሚ ባሕርይ የእድገት መርሆ ነው። የክርስቶስን ትዕዛዝ በመታዘዝ የሚኖሩ ቤተክርስትያናት መንፈሳዊ እድገትን ይለማመዳሉ መለማመድም አለባቸው። ታላቁም ተልዕኮ በማቴ28:19-20 ይህንን ያረጋግጥልናል። ***«ስለዚህ ሂዱና ሕዝብን ሁሉ በስብ በመሐደና በመጎደል ቅዱስ ስም ሕያመመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ ሕያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት ሕደርጉለቸው ስነሆም እኔ ስከአንሰም ፎፃሜ ዶረስ ከስናንተ ጋር ነኝ።»***

ይህ ተልዕኮ በታሪክ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ደቀመዝሙር ማድረግ የማይቻል ለመሆኑ የሚከፍተው ቦታ የለም። ተልዕኮው ይህ ቀረሽ የማይባል ነው በመሆኑም በውስጡ የመሳካት ቃል ኪዳን አለው።

ደቀመዝሙር የማድረጋችን መጠን ከትውልድ ትውልድ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ መሠረት ሊለያይ ይችላል። አንዳንድ አማኞች በታላቅ የመነቃቃት ዘመን ሊኖሩ ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ ለእውነት ከፍተኛ ተቃውሞ በሚደረግበት ዘመን ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንዶቻችን መቶ እጥፍ፣ አንዳንዶቻችን ስልሳ፣ አንዳንዶቻችን ደግሞ ሠላሳ እጥፍ ፍሬ እናፈራለን (ማቴ13:23)። መጠኑም የሚወሰነው በጌታ እጅ ውስጥ ነው። ነገር ግን የምናመርተው ምርት ብዙም ይሁን ወይም ጥቂት ለጌታ ቤተክርስትያናት ሁልጊዜ የነፍሳት የአዝመራ ውጤት አለ። እንዲሁም እኛ ደቀ መዝሙር ለማፍራት እስከጣርን ድረስ የሥራው ባለቤት ጌታ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ነው።

በዚህ ትምህርት ውስጥ ያለውን ማበረታቻ የምንወስድ ከሆነ በመሠ ረቱ ዘር የመዝራት ጊዜ እንዳለ ማወቅ አለብን። ጌታ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ ዘር የመዝራት ወቅት ደቀመዝሙር ከማድረግ ሥራ ጋር ይመሳሰላል። የመዝራትና የማጨድ ምሳሌ የሚያስጠነቅቀን ነገር ቢኖር አጥቢያ ቤተክርስትያን የመዝራትና የመትከል ጊዜ በሚገባ እንደምትለማመድና ከዚያም የማጨድ ጊዜ እንደሚከተል ነው። ***«ባንዘሪም በጊዜው ስናጭዳበንና መሰላም ሥሬን ስመስሬቶ ስንታክት»*** (ገላ6:9)።

ሐዋርያው ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች የተናገረው በቆሮንቶስ ስለራሱ የስብከት ሥራና ስለ ተከታዩ አገልጋይ ሥራ ነው። ***«እኔ ተከለሁ ስዶሎስም ስመጣ ነገር ግን ስግዚስብሔር ያሳደገ ነበር ።»*** (1ቆሮ3:6)።

በቆሮንቶስ ሐዋርያው ጳውሎስ ከአጵሎስ ያነሰ ፍሬ እንዳለው ያየ ይመስላል። ይህም የሚያረጋግጠው በወንጌል ሥራ የመዝራት ወራት መኖሩን ነው።

ይሁን እንጂ፣ በቤተክርስትያን ውስጥ የሚታየው እድገት ታላቁ ተ

ልዕኮ የመከናወኑ አስፈላጊ ምልክት ሆኖ ነው። ስለሆነም የቤተክርስትያን ምሳሌዎቹ በድጋሚ ይህንን መርሆ ያረጋግጡልናል ማለት ነው። ለምሳሌ፡- አካሉ በኤፌ4፡16 ላይ በጣም ግልጥ የሚያደርገው የሚያድግ አካል መኖሩን ነው። በሕንፃውም ምሳሌ የምናገኘው የሚያድግ ሕንፃ የግንባታው ሥራ ሁልጊዜ የሚያድግና የሚቀጥል መሆኑን ነው (ኤፌ2፡21)። እንደ ቤተሰቡም ምሳሌ እድገትን በሚገባ ግልጥ የሚያደርግ የለም። በተመሳሳይ መንገድ መንጋው ሁልጊዜ ይሰበሰባል። የወይኑ ግንድ እንደሌሎቹ እፀዋት ሁሉ እድገቱ በፍጹም ያቆመ አይደለም። ምክንያቱም እድገቱና ማፍራቱ የሕይወት መሠረታዊ ክፍሎች ናቸውና።

በሁሉም የቤተክርስትያን ምሳሌዎች ውስጥ በተግባር እንደታየው ለእድገት፣ ለቀጣይ እድገትና ለመስፋፋት ግልጥ የሆነ ማስረጃ አለ። ይህም የሚያረጋግጥልን የእግዚአብሔር ፈቃድ የእሱ አጥቢያ ቤተክርስትያን በመዝራትና ታላቅ የነፍሳት አዝመራ በማጨድ ቀጣይ ሥራ ሁኔታ ውስጥ ሁልጊዜ መኖር ያለባት መሆኑን ነው።

እንግዲህ እኔ ልቀላቀላት የምታስፈልገኝ ቤተክርስትያን እነዚህን የእውነተኛ የወንጌል - ቤተክርስትያንን አራት መሠረታዊ መርሆዎች የምታውቅ መሆን አለባት።

የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ

ከዚህ በላይ ያየናቸው አራት መርሆዎች የአጥቢያ ቤተክርስትያንን ባሕርይ የሚቀርፁ ናቸው ነገር ግን የአጥቢያ ቤትክርስትያን ዓላማ በትክክል ምንድነው? የአጥቢያ ቤተክርስትያን ጠቅላላ ባሕርይ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ባሉ ስድስት ቁጥሮች ላይ ተገልጧል፣ ይህም በሐዋ2:42-47 ነው። አሳቡንም በቀላሉ ለመያዝ ያመች ዘንድ ከዚህ በሚከተሉት አራት ርዕሶች ሥር ተቀምጧል።

የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማዎች :—

1. በኅብረት አምልኮ ላይ መሳተፍ፣
2. በምድር የመንግሥቱ ሰማይ ማኅበረ-ሰብ አባላት መሆን፣
3. ወንጌል ማሰራጨትና የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር፣
4. አማኞች ስጦታቸውንና ያላቸውን ሁሉ አሰባስበው የጌታን አገልግሎት እንዲያከናውኑ መንገድ መሆን ።

1. አምልኮ

የመጀመሪያው የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ የኅብረት አምልኮን ማከናወን ነው። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ያለው የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ፣ በአምልኮ ላይ ስለመሣተፍ ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል። በኅብረት አምልኮ ውስጥ ልዩ የሆነ ጠቃሚ ነገር አለ ያም የዘላለም ዋና አሳብ ሆኖ ለዘላለም የሚቀጥል መሆኑ ነው። የእግዚአብሔር መላእክትም በሙሉ ታላቅ የሆነ የዝማሬ ምስጋናን በማሰማት አብረው እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ በቃሉ ውስጥ እናነባለን።

የምስጋናም ክብር መገኘት ያለበት በጥልቀትና ከልብ እንዲሁም አብረው በሚተባበሩት ሕዝቦች ብዛት ጭምር ነው። ስለዚህ አንዱ የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዋናው ተግባር ሁሉን ቻዩን እግዚአብሔርን ሥርዓት ባለው፣ በተቀናጀ፣ ማኅበረ-ምዕመናዊ አምልኮ ለማምለክ መንገድ መስጠት ነው።

በነገራችን ላይ የኅብረት አምልኮ ከፍተኛ ኃይል ያለው ምስክርነት ነው። ይህ የኅብረት አምልኮ ዓለምን የሚማርክ ከሆነ፣ እንዲህ ዓይነቱ የሚማርክ ምስክርነት በግል ከሚደረግ አምልኮ አይመጣም ምክንያቱም የግል አምልኮ በጣም በግል የሚደረግና የምስጢር እንቅስቃሴ ነውና። ከሰው የትዕቢት ችግር የተነሳ በአደባባይ መጸለይና በግልጥ ምጽዋት መስጠት በጌታ የተወገዘ ነው። የተሰበሰቡ አማኞች አምልኮ ግን አስፈላጊ የሆነ የትሕትና ድርጊት ያለበት ነው። የተሰበሰቡ አማኞች ለጌታ ልባቸውንና ነፍሳቸውን የመስጠታቸው እውነታ፣ የእሱ የሕልውናው እውነት እንደተ ሰማቸው አድርገው እርሱን ማክበራቸውና መፍራታቸው እንዲሁም ከክብሩና ከኃይሉ መጠቀማቸው ሁሉ ኃይለኛ የሆነ ምስክርነት ነው።

እኛም እንደ ቤተክርስትያን አባላት ልንፈፀማቸው የሚገቡንን አንዳንድ ተግባራት ከዚህ ውስጥ ሊፈልቁ ልናይ እንችላለን። እግዚአብሔርን እንደሚገባ ለማምለክ በማለዳ መጠናቀቅና ለአምልኮው አገልግሎት በመንፈስ መዘጋጀት አለብን። ችግሮቻችንን ማስወገድ፣ በጌታ ፊት ኃጢአታችንን

መናዘዝ፣ እንዲሁም ልባችንን ለምስጋና ማዘጋጀት አለብን::

2. የመንግስተ ሰማይ ማኅበረ ሰብ

ሁለተኛው የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ በምድር ላይ በመንግሥተ ሰማይ ያለውን ዓይነት ማኅበረ-ሰብ እንድትሆን ነው:: በመሆኑም የክርስቶስ የሆኑ፣ ለእርሱ ታማኝና ታዛዥ የሆኑ፣ እውነተኛ የሕዝቦች ቤተሰብ ናት:: የእርሱ ሕዝብ የአንድነትን የፍቅርንና የመዋደድን ውበት የሚያሳዩ ቤተ ሰቦች ሆነው መሠራታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

አጥቢያ ቤተክርስትያን የታቀደችው አስደናቂ ነገር እንድትሆን ነው:: በመሆኑም ሕይወትንና ኃይልን፣ ፍቅርንና ተወዳጅነትን፣ በማሳየት እና እርስበርስ እየተጋገዙ አንዳቸው ለአንዳቸው እንክብካቤ ከሚያደርጉት አባላቶቿ ጋር አስደናቂ እንድትሆን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ17 ላይ እንደጸለየው ቤተክርስትያን የታቀደችው የእርሱ ኃይልና ምስክር እንድትሆን ነው:: እሱ የጸለየው ሁላችን በእርሱ በሆነው እምነት አንድ መሆናችንን ዓለም ያውቅ ዘንድ ነው:: ከወንጌል አገልግሎታችን ጎን ለጎን የአጥቢያ ቤተክርስትያን አስደናቂ ባሕርይ የታቀደው ሕይወቷንና አካሄዷን ለመመልከት ዕድል ላገኙት ሁሉ ጥልቅ የሆነ ስሜት እንድታሳድር ነው:: ***«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለእርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ ::»*** *(1ጴጥ2:9)*::

በአዲስ ኪዳን ጊዜ የነበሩት የቤተክርስትያን አባላት ራሳቸውን ያዩ የነበረው ሙሉ ለሙሉ አንዱ የሌላው እንደሆነ አድርገው ነበረ:: ይህንንም እውነት በኤፌ2:19-22 ውስጥ ያለው ቃል ይገልጠዋል:: ***«እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች ለደደባችሁም:: በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: በእርሱም ሕንፃ ሁሉ ስቦተጋመመ በጌታ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንዲሆን ያድጋል በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ ለብራችሁ ተመሬላችሁ::»***

እንደዚህ ዓይነት የቤተሰብ መንፈስ ለማደራጀት የእግዚአብሔር ቃል ለአጥቢያ ቤተክርስትያን የሥርዓትን መንገድ፣ ሥነ-ሥርዓትንና አስተዳደርን ሰጥቷል:: ይህም ስለአስተዳደር የበላይ ተመልካችነትና የቢሮ ኃላፊነት ብዙ በተጠቀሰባቸው እና የመጋቢነት መልእክቶች ተብለው በሚጠሩት የጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ግልጥ ነው::

በዓለም ላይ ከአምባ ገነን እስከ መጨረሻው ሥርዓተ አልበኝነት ድረስ ብዙ የአገዛዝና የአስተዳደር ዓይነቶችን እናያለን:: ታዲያ ለአጥቢያ ቤተ ክርስትያን ምን ዓይነት አስተዳደርና ሥርዓት ነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተሰጠው? የአጥቢያ ቤተክርስትያን አስተዳደር የስምምነት አስተዳደር ነው:: ምክንያቱም በቃሉ ላይ የአጥቢያ ቤተክርስትያን መሪዎች በአባላት ስለሚመረጡ አስተዳደሩ የስምምነት አስተዳደር ነው:: በመሆኑም በመጽሐፍ ቅዱሳዊው የአጥቢያ ቤተክርስትያን አስተዳደር ውስጥ አስደናቂ የሆነ ሚዛን አለ:: ይህም ሊታይ የሚቻለው በመጀመሪያ የሚቃረኑ የሚመስሉ አሳቦችን በሚገባ በማጤን ነው::

አዲስ ኪዳን በአንድ በኩል «የቤተክርስትያን ስብሰባ» ቃላት ብለን የምንጠራቸው የእግዚአብሔር ቃል *«የጥቅስ ቤተሰብ» አሉት። እነዚህም ጥቅሶች የሚሉት የአጥቢያ ቤተክርስትያን አባላት በሙሉ በቤተክርስትያን ስብሰባው ላይ በመገኘት. በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው ነው። ኃላፊነቶቹም የሚያካትቱት ብዙ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን መፍቀድ፣ የቤተክርስትያን መሪዎችንና ሚሽነሪዎችን መሾም፣ እንዲሁም አባላትን የመቀበልንና የማስወገድን ጉዳይ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያ ሲታዩ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚቃረኑ የሚመስሉ «የጥቅስ ቤተሰብ» የተጻፈባቸው ክፍሎች አሉ። ይህ ሁለተኛው የእግዚአብሔር ቃል «የጥቅስ ቤተሰብ» (ብዙ ጊዜ በተመሳሳይ መልእክቶች ላይ) የሚናገረው በቤተክርስትያን ስላሉ «የቤተ ክርስትያን አስተዳዳሪዎች» ነው።

የቤተክርስትያን አባላት ለሚገዟቸውና ለሚያስተዳድሩዋቸው ነፍሳቸውንም ለሚጠብቁት ራሳቸውን ማስገዛት እንዳለባቸው ታዘዋል። ብዙ ዎቹ ጥቅሶች እንደሚናገሩት መሪዎቹ የቤተክርስትያንን ጉዳይ ሊመሩና ሊያስተዳድሩ ተሾመዋልና ሥርዓትንም ለማስጠበቅ ልዩ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል።

በመሆኑም እነዚህ ሁለት «የጥቅሶች ቤተሰቦች» እርስ በእርስ አይቃረኑም ሁለቱም አብረው በመሆን የሚያሳዩት ነገር ቤተክርስትያን በእግዚአብሔር በተሾሙት የቢሮ ኃላፊዎች የመመራቷን መርሆ እየጸናችበት አባላቱ በሙሉ ደግሞ አንዳንድ ታላላቅ ውሳኔዎችን በመወሰን ይሳተፋሉ የሚለውን ሌላውንም መርሆ ነው። አጥቢያ ቤተክርስትያን የመንግሥቱ ሰማይ ማኅበረ-ሰብ ሆና የምትቀጥልበት አንዱ መንገድ ይህ የመሪነትና የአባልነት ማለትም የሁለቱም የሙሉ በሙሉ ኃላፊነት ውብ ሚዛን መኖሩ ነው።

ገደብ የሌለው መሪነት የለም

አጥቢያ ቤተክርስትያን በእግዚአብሔር ርስት ላይ ጌትነትን የሚያሳይ ገደብ የሌለው የቢሮ ኃላፊዎች መሪነት ሊኖራት አይችልም። ነገር ግን ቤተክርስትያን የሚኖራት መሪ በቤተሰብ ውስጥ ያለ እንዲሁም ለቤተሰቡ ራሱን የሰጠና ይህንንም ያረጋገጠ ነው። የቤተክርስትያን አስተዳዳሪዎች የሚያስተዳድሩትና የሚመሩት ሙሉውን የእግዚአብሔርን ቤተ ሰብ አንድ ወጥ ወደሆነ መንፈሳዊ ዓላማና ፍላጎት ነው።

ይህም የመቀባበል ዓይነት አመራር ነው። በመሆኑም ከውስጥ የሚወጣ እንጂ ከላይ ከመሪዎቹ በተዕእኖ መልክ ወደ ታች የሚፈስ አይደለም። ስለዚህም በአካሉ ውስጥ በመኖርና በምሳሌነት የሚሆን አመራር ነው።

---

*«የጥቅስ ቤተሰብ» [family of verses]: - በተለያየ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልክት ክፍል ውስጥ ተመሳሳይ አሳብን የሚናገሩ የጥቅሶች ዓይነቶች መኖራቸውን ለማሳየት ነው። ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሰው የቤተክርስትያን አባላትን ሥራና ተግባር እንዲሁም የመሪ ዎችን ሥራና ተግባር የሚገልጡትን ዓይነት የጥቅስ ክፍሎችን ነው።

ይህንን የአመራር ሚዛናዊነት የቤተክርስትያን ስብሰባ ሲደረግ በግልጥና በትክክል እንመለከተዋለን። ለአባላት ስብሰባ የሚቀርበው አጀንዳ ተራ የሆነ ትንሽ ነገር ወይም የዕለት ተዕለት የቢሮ ሠራተኞች የሚሠሩት ጉዳይ መሆን የለበትም። አባላት መሰብሰብ ያለባቸው አዳዲስ አባላትን ለመቀበል፣ መሪዎችን ለመሾም፣ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ለመመርመር፣ ጎብረቱ በሙሉ የሚካፈልበትን ጥረትና ወጪዎች፣ የሚያጽድቀውንና ለጸሎት የሚሰጥበትን ጉዳይ፣ ባለአደራነቱንና የሚደክምበትን ሁሉ አብሮ ለማየት ነው። በነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ላይ የመነሻ አሳቡ በመጀመሪያ በመሪዎቹ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት። ከዚህ የተለየ ሥርዓት ማምጣት በጌታ ቃል ላይ ያለውን የአመራር ክፍል ትእዛዝ መጣስ ማለት ነው።

ጥልቅ ጎብረት

የመንግሥተ ሰማይ ማጎበረ-ሰብ መሆን ማለት፡- የጎብረትን ሥራ፣ ፍቅርን፣ ወዳጅነትን፣ ለጋራ ጥቅም እርስ በእርስ መገሣሠጽን እና የእርስ-በእርስ ሽክም መሸካከምን (ገላ6፡1) ተግባራት ሁሉ ማሟላት ማለት ነው። እንደ ቤተክርስትያን አባላት የኛ ጥሪ ጓደኝነትን (ወዳጅነትን) አብሮ በመዝራት አንዳችን ለሌላው ፍላጎት የሚሰማን ልንሆን፣ አንዳችን ለሌላው ልናስብና ልንጸልይ፣ በአጭሩ በተቻለን መጠን ሁሉ ራስ ወዳድ ሳንሆን ከሌላው ጋር ጎብረት የምንፈጥር እንድንሆን ነው። የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስትያን ለራሳችን ደስታና ጥቅም ከመቀየር አሰቃቂ ፈተና መቆጠብ ወይም መራቅ አለብን። በተለይ በወጣቶች አካባቢ በድንገት የመዝናናት እንቅስቃሴ ላይ የመሳብ ማዕበል ሊነሳባቸው ይችላል። በመሆኑም በጌታ ያለው ጎብረት ለአምልኮና በመንፈስ ለማደግ መሆኑ ይቀርና ክርስትያናዊ ለሚመስሉ ደስታዎች ብቻ የሚሰማማ ይሆናል።

ነገር ግን ሁላችንም ዘሩን ዘሪዎች በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያለማቋረጥ ራሳችንን መጠየቅ አለብን «እኔ ምን ሠርቻለሁ? (ምን ጨምሬአለሁ?) ለጌታዬስ ቤተክርስትያን በምን መልኩ ጥቅም እሰጣለሁ?»።

3. ቃሉ

ሦስተኛው የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ ወንጌልን በማሰራጨትና ቃሉን በማስተማር ጌታን በዓለም ፊት መወከል ነው። በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስትያን ቃሉን በማጥናት እንዲሁም በኃይለኛ የግል ምስክርነትና የስብከት ሥራ ተጠምዳ እንደነበረ አይተናል። «***በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ ይዋጡ .....***» (ሐዋ2፡46)።

በቤተመቅደስ ምን ያደርጉ ነበር? በዚያ ቤተመቅደስ ውስጥ በእርግጥ እያመለኩ አልነበረም። ምክንያቱም «***በጢስቸው ስንጸሬን ይየቀረቡ***» ብሎ ቃሉ ይቀጥላልና ነው። በቤተመቅደስ ውስጥ የነበሩበት ምክንያት ለሰዎች ለመመስከር፣ ለሰዎች ስለጌታ ለመንገር ነበር። (በተለይ ሰው ሁሉ ከየአገሩ በሚሰበሰብበት በጸንጠቆስጤ በዓል ጊዜ)።

ቃሉን ለማስተማርና ወንጌልን ለማስፋፋት የአጥቢያ ቤተ ክርስትያንን አደረጃጀት ይጠይቃል። አንዳንድ ሰዎች (ጥቂቶች ቢመስሉም

እንኳ) ለማስተማርና ለመስበክ የተለየ ስጦታ አላቸው። ሌሎች ደግሞ ሌላ ዓይነት ስጦታና ችሎታ አላቸው። አዲስ ኪዳን ለወንጌል ስርጭት የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በብቃት ሊያስተምሩ የሚችሉ ሰዎችን እድናሠለጥን ያዘናል (2ጢሞ2:2)። ይህም ትእዛዝ ያለአጥቢያ ቤተክርስትያን መኖር በእርግጥ ሊከናወን የሚችል አይደለም።

እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ የሚያሳየው ቤተ ክርስትያን ካልኖረች በብቃትና በጥራት ሊከናወኑ የማይችሉ እንቅስቃሴ ዎችን ነው። ያለእንደዚህ ዓይነቱ ስብሰባ የጋራው አምልኮ ሊከናወን እንደማይችል በጣም ግልጥ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ያለእንደዚህ ዓይነቱ ስብሰባ በምድር የመንግሥተ ሰማይ ማኅበረሰብ፣ የመንፈሳዊ ቤተሰብ ባሕርይ ፈጽሞ ሊታይ አይችልም። እንደዚሁም ያለ ቤተክርስትያን ብዙ አስተማሪዎችንና ሰባኪዎችን እንደሚገባ መደገፍ አንችልም።

የታላቁን ተልዕኮ ትእዛዝ መቀጠልና የቤተክርስትያን አባልነትን ተ ግባራት ማካሄድ የሚጨምረው ነገር ቃሉን ለማስተማርና ለመስበክ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማሟላትንም ነው።

4. የተውጣጣ ምንጭ

አራተኛው የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማ «ለክርስቶስ አገልግሎት የክርስትያኑን ሕዝብ ጥሪት ሁሉ ማሰባሰብ» የሚለው ነው። ይህም የቤተ ክርስትያንን አባላት ችሎታ ማጠናከርና የነሱን ጥረት በተገቢው መንገድ ማደራጀትና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቀጣይ ትውልድ ማሠልጠንን ይጨምራል። አሁንም እነዚህ ነገሮች ያለአጥቢያ ቤተክርስትያን በሚገባ ሊከናወኑ አይችሉም። ክርስትያን ሕዝቦች ከአንድ ላይ የሚያጣምራቸው አንድ ነገር ማለትም አጥቢያ ቤተክርስትያን ሳይኖር ያላቸውን ሁሉ ለአገልግሎት አንድ ላይ ማሰባሰብ አይቻልም። እንዲሁም የነሱ ችሎታና ሙያ በብቃትና በሥልጠና ተገቢውን መበረታታት አግኝቶ ለአገልግሎትና ለጋራ መጽናናት አይውልም።

ለምሳሌ ሁላችንም ግለኝነት ላይ ትኩረት ሰጥተን አባልነትን ችላ ብንል፣ እንዲሁም ለምሳሌ አንድ ሰው በጉብኝት ሥራ በጣም ጥሩ ቢሆንና ነገር ግን ወንጌልን በመግለጥና የተቸገሩትን በመምከር በኩል ደካማ ቢሆን፣ እንዲህ ዓይነቱ በራሱ የሚሰራው ሰው ወዲያው ከፍተኛ ችግር ውስጥ መውደቁ የማይቀር ነው። ያ ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ሕይወት ባለው ኅብረት ውስጥ ከሰራ ግን የእሱ የተለየ ስጦታ ሊበረታታ እንዲሁም ከፍተኛ ጥቅምና አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል። ስብከቱንና ምክር መስጠቱን ሌሎች ሊሠሩት ይችላሉና።

ሥጦታን ማሳደግ

ተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ የግል ችሎታዎቻችንና ስጦታዎቻችን ወደ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊመጡ የሚችሉት አብረን ከሠራን ብቻ ነው። የአጥቢያ ቤተክርስትያን ሥራ የእኛን ጥሪቶች ማሰባሰብና የተለያዩ ስጦታዎቻችንን በአንድ ላይ በማምጣት የተያያዘና ሙሉ የሆነ ትልቅ አገልግሎት ለጌታ መስጠት ነው። ብዙዎቻችን ከወንጌል ሠራተኞች ጋር ሕይወት ባለው ኅብ

ረት ውስጥ ከሌለን ወዲያው ተስፋ እንቆርጣለን፣ በኛ ትንሽ ኃይልና ጥረት የሚደረገው ግለሰባዊው እንቅስቃሴ ቶሎ ይዳከማል፣ እኛንም የሚቃወሙን ኃይላት ይከብዱብናል። እኛ ያለን የባለአደራነታችን ጉዳይ በአባልነት ባለንበት በዚች በአጥቢያ ቤተክርስትያን አገልግሎት ውስጥ ተጨምሯል። እዚያም ቤተክርስትያን ውስጥ ያለንን የእኛን ነገር ልናቀርብና የሙሉ ጊዜ አገልጋይ የሆኑትን የመደገፍ ተግባር አለብን። ይህንን የሚያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ክፍል 1ቆሮ9 በተለይ ቁ6-14 ላይ ነው።

የአጥቢያ ቤተክርስትያንን አባላት ችሎታዎች ሁሉ ጥቅም ላይ ለማዋል ብዙ ነገር ማደራጀት እንደሚቻል አሁን ግልጥ ነው። ቤተ ክርስትያናት በሰዋዊ አደረጃጀት መደገፍ የለባቸውም። ይሁን እንጂ በዚህ በኩል ብዙ ሊሠራ የሚችል ነገር አለ። ማለትም ችሎታው ያላቸው የቤተ ክርስትያን አባላት ሁሉ ለአገልግሎት እንዲሠለጥኑ መደረጋቸው ነው።

ለቤተክርስትያን መሪዎችና ሰባኪዎች ታላቅ ፈተናቸው ከዚህ ታላቅ ውስብስብ ተግባር ማፈግፈግና ድርጅት ወይም መዋቅር አልባ ወደሆነ የሰባኪ-ምዕመን አገልግሎት ደረጃ መውረድ ወይም ዝቅ ማለት ነው። አንድ አገልጋይ የሰንበት ትምህርት እያካሄደ እስካለ ድረስና በቤተክርስትያኒቱ ውስጥ መሠረታዊ የቤተክርስትያን መምሪያዎች ተዋቅረው እስካሉ ድረስ ሊታሰብበት የሚገባ ጥቂት ነገር አለ ማለት ነው። የተቻለንን ያህል ትልቅ አውትሪች እንዲኖር የማድረጉ ትግልና ከማኅበረ-ሰቡ ጋር ግንኙነት አድርጎ ሁሉን ወደ ውጤታማ እንቅስቃሴ ለመምራት የሚታሰበው አሳብ የማያዛልቅ ወይም ከባድ መስሎን ተስፋ መቁረጥ የለብንም።

ነገር ግን ይህን የአጥቢያ ቤተክርስትያንን የመጨረሻ ዓላማ ለማክበር መጣር አለብን። ያሉን ጥሪቶች ተሰባስበው፣ ችሎታዎቻችን አድገው፣ አባላቶቻችን ሁሉ የአጥቢያው እውነተኛ የጌታ ሠራዊት መሆን ይችላሉ።


ትምክትን መቀነስ

ከአገር አቀፍ ድርጅቶች በተፃረረ መልኩ አንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስትያን ጥቅም የሰዋዊ ኩራትንና የድርጅት በሽታን መቀነሱ ነው። የሰው አእምሮ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ በዚህ ነጥብ ላይ እጅግ በጣም ይወሰዳል። ይህም ከዳኑትም ሰዎች መካከል እንኳ ጭምር ነው። የሰው አዕ ምሮ ትልልቅ ድርጅቶችንና የብዙ ተከታይ አጀብን ይወዳል። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ደግሞ እጅግ በጣም መጥፎ ነገርን ከሰዎች ውስጥ ያመነጫሉ።

ስለዚህም የብዙ ቡድን መሪዎች በሚመሯቸው ላይ ጌታ መሆን እንዲሁም በክንዋኔ ስኬት ኩራት ይያዙና ኃይል ማሳየት ይጀምራሉ። እንፈነቀላለን የሚል ፍርሃት ያድርባቸዋል። በመሆኑም ቦታቸውን እንዳይቀሙ ችሎታ ያላቸውን ሌሎችን ይቃወማሉ። በሰው አእምሮ ውስጥ የብዙ ሕዝብ ቡድን መቆጣጠርን የሚያስወድድ እንደ በሽታ የሆነ በውስጡ የተቀመጠ አንድ ነገር አለ። ይህም እንደ በሽታ የሆነው ነገር ወዲያውኑ የድርጅቱን ዓላማ እና ጠቀሜታ እያሳነሰ የራስ ክብርንና ቦታን በመጠበቅ ላይ በጣም ትልቅ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚህ ዓይነት ሥጋዊ ነገሮች የሱን ቤተ ክርስትያን ሥራዎች እንዳይበክሉ ወስኗል። በመሆኑም ሁሉን ወደ ጎን ጠርጎና አስወግዶ እያንዳንዷ ቤተክርስትያን ራሷን የቻለች በራሷ የምትመራ አጥቢያ ቤተክርስትያን እንድትሆን ሾሟታል።

ጌታ ኢየሱስ የእሱ የአገልግሎቱ ቢሮ ኃላፊዎች ሲያገለግሉ ሕዝቡ በጣም በቅርብ ተጠግቶ እንዲያውቃቸው፣ የሚያስኮራቸውና የራሳቸው የሚሉት ትልቅ ነገር እንዳይኖራቸው፣ የድርጅታዊ አእምሮ ማዳበር እንደሌ ለባቸው ያደረገበት እንደ አጥቢያ ቤተክርስትያን ያለ በጣም ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ የለም። እኛም የአዲስ ኪዳንን የአጥቢያ ቤተክርስትያን ግሩም ምሳሌ የምናደንቅበት፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስትያን ክልል ውስጥ ብቻ የምንሆንበት፣ እንዲሁም ከሰው በጣም መጥፎ ነገርን ማለትም ትምክህት የሚያመጣውን ትልቅ ዲኖሚኔሽንና ውስብስብ ድርጅትን የማንመሰርትበት ዋናው ምክንያት ይህ ነው።



በሐዋ2:42-47 የታዩት ዘጠኙ እንቅስቃሴዎች ከአራቱ የአጥቢያ ቤተክርስትያን ዓላማዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በስዕላዊ መግለጫ።

የቤተክርስትያን አባልነት ሕግጋት

ጆን ፍሊቸር (1729-1785)

በብሉይ ኪዳን *«የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ እግዚአብሔርም አደመጠ ሰማም፣ እግዚአብሔርንም የሚፈሩ ስሙንም ሲያከብሩ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተጻፈ።»* (ሚል3:16) ተብሎ የተጻፈውን እናነባለን:: በወንጌሎች ውስጥ ደግሞ በራሱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተጠሩ «የሰዎች ስብስብ» እንደነበሩ ተመዝግቦልናል:: እሱ ካረገ በኋላ *«እነዚህ ሁሉ ... በአንድ ዐብይ ሆነው ሰዘውትር ጸንተ ነበር።»* (ሐዋ1:14):: የጰንጠቆስጤም ዕለት በመጣ ጊዜ ሁሉም እንደገና «*ሁሉም በአንድ ዐብይ ሰብረው ሳሉ*» (ሐዋ2:1) የጌታ ኃይል ወርዶ ቁጥራቸው እጅግ በጣም ከጨመረ በኋላም *«በሐዋርያትም ተምህርትና በኅብረት እንጀራንም በመቁረስ በየዘውትሩም ጸንተ ነበር፣ ... ያመኑትም ሁሉ ዐብረው ነበረ፣ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት ሰጸደሩ።»* (ሐዋ2:42 እና 44):: ይህም ያ በጣም የተቀራረበ ኅብረት ሐዋሪያቱ በተደጋጋሚ ይሰጡት ለነበረው ትእዛዝ ምስክር መሆኑ የማያጠራጥር ነው:-

. *«በእንዳንዶችም ዘንድ ሰማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን ስንተው እርስ በእርሳችን እንመካከር እንጂ ደዐቂነም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ ዐብዕማችሁ ደህነ ሰድርጉ»* (ዕብ10:25)::

. *«የእግዚአብሔር ቃል በመሳት ጸኑርባችሁ በሞበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ እስተምሪና ገሥጹ በመዝሙርና በዘማሪ በመንፈሳዊም ቀኔ በዘጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ»* (ቆላ3:16)::

. *«ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ እርስ በእርሳችሁ ተመካከረ ሰንዱም ሰንዱም ሲሳውን ያንጸው :: .... መንድሞች ሆይ እንመከራችኋለን ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው ደፍረት የሲሳቸውን ሰዘንቶቸው ሰደካሞች ተጉሳቸው ሰሙን ሁሉ ታገሡ።»* (1ተሰ5:11 እና 14)::

በነዚህ የሐዋርያት ትእዛዛት እንዲሁም በዘመናት የነበሩ መንፈሳዊ አማኞች በፊት ለፊታችን ባስቀመጡት ምሳሌ በመበረታታት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን ለመምሰል በተጠቀሱት መስፈርቶች መሠረት የቤተክርስትያን አባላት ቅንነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው:: ይህም ከዚህ በሚከተሉት ሦስት ርዕሶች ስር ሊጠቃለል ይችላል:-

1. ክፉ ማድረግን አቁሙ: - (ኢሳ1:16. ሮሜ12:9)
2. መልካም መሥራትን ተማሩ: - (ኢሳ1:17. ሮሜ12:9)
3. እግዚአብሔር በሰጠን አገልጋዮች በኩል ከእግዚአብሔር ብርሃንና በረከትን ፈልጉ: - (ኢሳ55:6. 2ጢሞ2:5)

ሀ. ክፉ ማድረግን ለቁሙ፡ -

1. ማንኛውም አባል ዓለማዊ መዝናናትን ዳንስን ወይም ቁማርን በመጫወት የዚችን ክፉ ዓለም ውበትም ሆነ ከንቱነት መከተልና በሷም መመራት የለበትም:: ማንኛውም ክርስትያን በጌታ ስም ሊደረጉ የማይገባቸውን የትርፍ ጊዜ እንቅስቃሴዎችን መከተል የለበትም:: (ኤፌ4:22. ሮሜ12:2. ገላ5:24-25. ቆላ3:17)::

2. ማንኛውም አባል ለግዴለሽነትና አስፈላጊ ላልሆነ የራስ ማሞላቀቅ እንዲሁም ለስንፍና ቦታ መስጠት የለበትም:: በተጨማሪም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውንና ለታይታ የሚሆኑ ልብሶችንም መልበስ የለበትም:: (1ተሰ5:23. 1ጴጥ2:11. 2ጢሞ2:3. 1ቆሮ9:27)::

3. ማንኛውም አባል ጥቅም በሌለው ወይም ክፉ በሆነ ንግግር ውስጥ መሳተፍ የለበትም:: እንዲሁም በቆሻሻ ንግግር ወይም በቀልድ በደለኛ መሆን ወይም ከሌሎች በስተጀርባ የሚናገር ሐሜተኛ መሆን የለበትም:: (ኤፌ4:29. 5:3. ይሁዳ1:8. ሐዋ23:5. ያዕ4:11)::

4. ማንኛውም አባል በሰው ጉዳይ ጣልቃ የሚገባ ወይም ለሌሎች ክፉ በመሆን በደልን በመበደል መገኘት የለበትም:: (1ጴጥ3:8. 4:15. 1ጢሞ5:13)::

5. ማንኛውም አባል የተሻለ ክርስትያንና ጥሩ ጎረቤት የማያስደርገውን መዝሙር መዘመርና መጽሐፍም ማንበብ የለበትም:: (ያዕ5:13. ኤፌ2:3. ቆላ3:16)::

6. ማንኛውም አባል በመግዛትና በመሸጥ ወይም በቅዳሜ ቀን የሚሠሩትን ወይም እስከ ሰኞ ሊተላለፉ የሚገባቸውን ነገሮች «በጌታ ቀን» ማለትም «በሰንበት» ቀን በመሥራት «የጌታን ቀን» ወይም ሰንበትን ማርከስ የለበትም:: (የአሥርቱ ትእዛዛት አራተኛው ትእዛዝ፣ ኢሳ58:13. ዘኁ15:32-36)::

7. ማንኛውም አባል እርኩሰትን በመፈጸምና በመጠጣት ጌታን የሚበድል መሆን የለበትም:: (ሮሜ13:13. ማቲ24:36-51. 1ተሰ5:6-8)::

8. ማንኛውም አባል መጣላት፣ ረብሻ መፍጠር፣ ክፉን በክፉ መመለስ፣ ጩኸትን በጩኸት መመለስ፣ ወይም ስድብን በስድብ መመለስ የለበትም:: (የአሥርቱ ትእዛዛት ስድስተኛው ትእዛዝ፣ 1ቆሮ5:11. 6:7. ሮሜ13:13)::

9. ማንኛውም አባል በንግድ ሥራ ላይ ቢሰማራ በሌሎች ጉዳት ወይም ኪሳራ ላይ የተመሰረተ ትርፍ ማትረፍ የለበትም ወይም በሱ ላይ እንዳይፈጸም የማይፈልገውን በሌሎች ላይ መፈጸም የለበትም:: (1ተሰ4:6. 1ቆሮ10:24. ሮሜ13:7)::

10. ማንኛውም አባል መንፈሳዊ ሥራን ሲሠራ መደበኛ ሥራውን ወይም ኃላፊነቱን መሥዋዕት አድርጎ ወይም በድሎ መሆን የለበትም:: ለክርስትያናዊ ሥራው የሚያውለው ጊዜ ከመደበኛ ሥራው ወይም ኃላፊነቱ

ላይ ተሰርቆ ሳይሆን ከትርፍ ጊዜው ወይም ከእንቅልፍ ጊዜው ተቀንሶ መሆን አለበት:: (2ተሰ3:8-12. 1ጢሞ5:14. ሮሜ12:11)::

ለ. መልካምን ለመስራት ተማሩ:-

1. ማንኛውም አባል በችግር ላሉ በሥጋ የሚያስፈልጋቸውን በመስጠት ማገልገል አለበት:: ይህም የታመሙትን በመጎብኘትና በችግር ያሉትን በመርዳት ጭምር ነው:: (መክብ4:10. ገላ6:2 እና 10. ማቴ25:35. ያዕ 1 : 2 7 ወዘተ)::

2. እያንዳንዱ አባል በሚችለው መጠን የሌሎችን ነፍስ ማገልገል አለበት:: ለመንፈሳዊ ነገር ምንም እውቀት የሌላቸውን በትዕግሥት በማነጋገር፣ የረከሱትን በዝግታ በመገሠጽ በኃጢአት የሚመላለሱትን በጥንቃቄ በማስጠንቀቅ ሁኔታ እንደተመቻቸለት ማገልገል አለበት (ሉዋ19:11. ዘዳ6:7. ዕብ3:13)::

3. እያንዳንዱ አባል ሥነ-ምግባር የጎደላቸውን ባለው ኃይሉ ሁሉ በመገሠጽ እንዲሁም በራሱ ውስጥ ባለው የተመሰገነ የሕይወት ምስክርነት በዙሪያው ያሉት ክፉ ባሕርያቸውን እንዲተው ወይም እንዲጥሉ ማድረግ አለበት:: (ኤፌ5:11. መሳ5:23. 1ሳሙ3:13. ያዕ5:19 እና20)::

4. እያንዳንዱ አባል በሥራው ላይ ከመጠን በላይ ትጉህ መሆን አለበት:: (ማቴ5:16. 1ጴጥ2:12. 2ቆሮ6:3)::

5. እያንዳንዱ አባል ራሱን በመካድ፣ መስቀሉን በየዕለቱ መሸከምና ዳግም እንደተወለደ ሰው ክርስቶስን መከተል አለበት:: እራሱንም ለወንጌል ነቀፋ በመስጠት በጌታ ላይ እንደፈጸሙት በጌታው ምክንያት በሱም ላይ ሰዎች ክፉውን ሁሉ በውሸት እንደሚናገሩበት በመገመት ወይም በመጠበቅ መሆን አለበት:: (ማቴ16:24)::

ሐ. ጌታ በመደባቸው አገልጋዮች በኩል በረከትን ፈልጉ:-

1. እያንዳንዱ አባል በቤተክርስትያኑ በሚካሄደው የእግዚአብሔር አምልኮ ላይ መሳተፍ አለበት (መዝ42:4. ሉቃ2:37)::

2. እያንዳንዱ አባል የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርትና ማብራራትን በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ መስማት አለበት (2ጢሞ4:2. ሮሜ10:17)::

3. እያንዳንዱ አባል ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በጌታ እራት ላይ መሳተፍ አለበት (ሐዋ2:46. 1ቆሮ11:24)::

4. እያንዳንዱ ወላጅ የሆነ አባል ቤተሰቡን ማገልገልና ልጆቹን በእምነቱ መመገብ አለበት (ዘፀ13:8-10. 14-16. ዘዳ6:6-9. ኢያ24:5. ምሳ22:6. ማቴ19:14)::

5. እያንዳንዱ አባል በግል የመጸለይ ተግባር ማከናወን ይኖርበታል፣ ቢያንስ ጠዋትና ማታ (መዝ119:164. ዳን6:13. ሐዋ9:11. ማቲ14:23)::
6. እያንዳንዱ አባል የጌታን ቃል ዘወትር ማንበብና ቃሉንም ማሰላሰል አለበት (ዘዳ6:7. መዝ1:2. ራዕ1:3. ዮሐ5:39. ሉቃ10:26. ሐዋ17:11)::

ወንድም ተብሎ የተጠራ ማንም ሰው ሴሰኛ ወይንም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ተጨቃጫቂ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካራም ቢሆን ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር ጎብረት ማድረግም ሆነ አብረን በአንድ ማዕድ መካፈል የለብንም:: (1ቆሮ5:11)::

ማንኛውም አባል ሥርዓት የሌለው፣ ሥራ ፈት፣ ዓለማዊ ባሕርይን የሚወድ፣ ወይም ትዕቢተኛ፣ በኃይል የመጨቃጨቅ ባሕርይ (ይህ ዓይነት ባሕርይ የቤተክርስትያን ሰላምና ፍቅር ታላቅ ጠላት ነውና) ያለው ሆኖ ቢገኝ በእርምት ቤተክርስትያን ሊገሰጽና ሊታረም ይገባዋል ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ተሰ3:14-15 ላይ:- «***በዚህ መልዕክት ለተሳከ ቃላችን ያማይታዘዝ ማንም ቢኖር ደዘን ተመልከቱት ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር ለተተባበረ:: ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥፁት እንጂ እንደ ጠላት ለተቁጠረ:::***» ብሎ የተናገረውን በማስታወስ ነው::

አባላት እርስ በእርስ ቅር እንዳይሰኛኙ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፣ የዚህም ዓይነት ስሜት በመካከላቸው መኖሩን እንደተገነዘቡ ወዲያውኑ ሳይዘገዩ መገላለጥ አለባቸው (ሮሜ12:9. ፊል2:1-3 ማቲ18:15-17)::

አባላት በውጪያዊ ሃይማኖትነት ላይ እንዳይታመኑ በተለየ ሁኔታ መጠንቀቅ አለባቸው:: ነገር ግን የእግዚአብሔር የትሕትና ፍቅር በልባቸው በሙላት ያድርባቸው ዘንድ እና የሃይማኖትን ኃይል መፈለግ አለባቸው:: ስለዚህ:- «***ወንድማማች መሆዳደ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ እርስ በእርሳችሁ ተከባበረ ... ... :: ደስ ከሚሳችሁ ጋር ደስ ደበሳችሁ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ:: እርስ በእርሳችሁ በለንደ ልዳብ ተስማሙ የትዕቢትን ነገር ለታስቡ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመከራት ተጹ:::***» (ሮሜ12:10እና15-16) በሚለው ቃል መሠረት መኖር አለባቸው::

የቤተሰብ ቃል ኪዳን

በቤንጃሚን ኪች

ይህ ዝነኛ የመንፈሳዊ አንድነት መሐላ እውነተኛ ቃል ኪዳን ሆኖ የተዘጋጀው በ1689 በለንደን በነበረው በፓስተር ኪች ታላቅ ጉባኤ ነበር። በነዚያ ጊዜያት ይህ ቃል ኪዳን በእያንዳንዱ የጌታ እራት ላይ ይነበብ ነበር። ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ በዘያው ቤተክርስትያን አሁን ሚትሮፖሊታን ታባርናክል ውስጥ ይህ የቤተሰብ ቃል ኪዳን እንዲጠበቅ አሁንም የአባላትን ሁሉ መሐላ ይፈልጋል።

እኛ በጌታ ፍርሃት አብረን ለመመላለስ የምንሻ፣ በእርሱ የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ አማካኝነት፣ የመተላለፋችንን ሁሉ ጥልቅና ከባድ ሃፍረት እንናዘዛለን።

በእግዚአብሔር ፊትና እርስ በእርሳችን ይህንን ስናደርግ በትሕትናና እኛ ራሳችን በራሳችን ጥቅመቢስ መሆናችንን በመረዳት መንፈስ ወይም ስሜት ውስጥ በመሆን ነው። በሐዋርያት ደንብ መሠረት፣ በቤተክርስትያን አስተዳደር ራሳችንን ለጌታ በመስጠት፣ እሱ አምላካችን ይሆን ዘንድና እኛም ሕዝቦቹ እንሆን ዘንድ፣ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት በምናገኝበት ብቸኛ ተስፋችን በሆነው በዘላለማዊው የእርሱ የነፃ የጸጋ ቃል ኪዳን መሠረት፣ ሊያፀድቀንና ሊቀድሰን እንዲሁም ሊያስተምረን ነቢያችን በሆነው፣ ሊቀ ካህናችን አድርገን በምንወስደው በተባረከው ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እርሱንም የተባረከውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሕግ ሰጪአችን ልንገዛለትና የቅዱሳን ንጉስ አድርገንም ልንወስደው፣ ለእድገታችን ለመጽናታችን እንዲሁም ለመጽናናታችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ለሆኑት ለቅዱሳን ሕግጋቶቹና ሥርዓቶቹ ልንስማማ፣ በዚህም እኛ ለእሱ ቅድስት ሙሽራው ሆነን በትውልዳችን ሁሉ እናገለግለው ዘንድና እጅግ በጣም እንደ ከበረ ሙሽራችንም የእርሱን ዳግም መገለጥ እንጠባበቅ ዘንድ ቃል እንገባለን።

በቤተክርስትያን በሚኖረው ጎብረት መንገድ ሙሉ በሙሉ በመርካትና በእያንዳንዳችን መንፈስ ውስጥ ባለው መልካም የጸጋ እውነት መጠን ለወንጌል ሥርዓት በትሕትና በመገዛት እንዲሁም በእንደዚህ ያለ መንፈሳዊ ጎብረት ውስጥ ካሉ ሰዎች የሚጠበቁትን ቅዱሳን ሥራዎች እና አገልግሎቶችን ሁሉ ለማድረግ እና በቅዱስ አንድነትና ጎብረት እራሳችንን በእውነት በማጣመር፦

1. በቅድስና ሁሉና እግዚአብሔርን በመምሰል፣ በትሕትናና በወንድማማች መዋደድ፣ ያለን ጎብረት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አርገን የመጠበቁ ነገር በእኛ ላይ እንደተጣለ ሁሉ፣ ለእኛም የሚመች ለሌሎችም የጌታ ሕዝቦች የተወደደ እንዲሆን በማድረግ ለመሳተፍና ለመመላለስ ቃል እንገባለን።

2. እግዚአብሔር ይህን ለእኛ ወይም ለማንኛችንም እስከገለጸልን ድረስ አንዳችን በሌላው ላይ ኃጢአትን ላለመፈጸም፣ እንዲሁም ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እርስ በእርስ ልንነቃቃ፣ ልናስጠነቅቅ ልንገሥጽ እንዲሁም በትሕትና አንዳችን ሌላችንን ልናገዝ፣ በዚህ በኩል ክርስቶስ እንድንጠብቅ ባስተላለፈልን ትዕዛዝ መሠረት ለእርስ በእርሳችን ንግግር ጥንቃቄ ለማድረግ ቃል እንገባለን።
3. ለዚች ቤተክርስትያን ማደግና ክብር፣ በውስጧም ለእግዚአብሔር መገኘት፣ በውስጧ ለእርሱ መንፈስ መፍሰስ፣ ለእርሱ ክብር እሷን ይጠብቃት ዘንድ፣ እናም በተለየ መልኩ አንዳችን ለሌላችን ለመጸለይ ቃል እንገባለን።
4. እርስ በእርስ ልንጠጋጋ፣ እንዲሁም እርስ በእርሳችን የጎበረት ወይም የአንድት ስሜት ሊኖረን፣ በሁሉ ሁኔታ በሁለቱም ማለትም በውጫዊም ሆነ በውስጣዊ አንፃር እግዚአብሔር በአሠራሩ እያንዳንዳችንን ባስቀመጠበት ነገር ሁሉ ውስጥ አንዳችን የሌላውን ሸክም ልንሸከም ቃል እንገባለን።
5. አንዳችን የአንዳችንን ድካም ውድቀትና መከራ በብዙ ርኅራኄ ልንሸከም ይህንንም ከቤተክርስትያን በስተቀር እንዲሁም በክርስቶስ ሕግ ካልተፈቀደ እንዲሁም በዚህ በኩል ልዩ የወንጌል ትእዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር፣ በውስጥም ላሉት እንኪንና ለሌላ ለማንም ላንገልጠው ቃል እንገባለን።
6. ለወንጌል እውነትና ለእግዚአብሔር አሠራር ሥርዓት ንጽህና፣ አብረን ለመጣር እናም በበኩላችን የመለያየት ምክንያት ላለመሆንና ምክንያትንም ለማጥፋት፣ የመንፈስንም አንድነት በሰላም ማሰሪያ ለመጠበቅ (ኤፌ.4:3) ቃል እንገባለን።
7. በጌታ ቀን (በሰንበት) እንዲሁም ጌታ እድልን በሰጠን በሌላ ቀን አብረን ለመሰብሰብ፣ እሱን ለማገልገልና ለማክበር እሱ በሚመለክበት መንገድ እርስ በእርሳችን ልንተናነጽ እንዲሁም የቤተክርስተያኑን መልካምነት ለመጠበቅ ቃል እንገባለን።
8. እንደ ችሎታችን መጠን (ወይም እግዚአብሔር በዚህ ዓለም መልካም ነገር ሁሉ እንደባረከን መጠን) ወንጌል ሰባኪዎች በወንጌል መኖር አለባቸው ብሎ እግዚአብሔር ስላዘዘ ከመጋቢያችን ወይም አገልጋያችን ጋር ልንነጋገር ቃል እንገባለን።

(በሕሊና ላይ ታላቅ ግዳጅን የሚጥል ከዚህ ቃል ኪዳን የበለጠ አሁን ሌላ ምን ነገር ይኖራል? ታዲያ ይህን የሚተላለፉ ሰዎች ኃጢአት ምን ያህል የከፋ ይሆን?)

ለነዚህና ለሌሎች የወንጌል ተግባራት በሙሉ እኛ እራሳችንን በትሕትና እንሰጣለን። ይህም ቃል በመግባትና ይህንንም ለማከናወን በማቀድ፣ የራሳችንን ደካማነት በመረዳት፣ ነገር ግን የእርሱ በሆንነው፣ ልናገለግለው በምንመኘው፣ በተባረከው በእግዚአብሔር ኃይልና ብርታት በመታመን ነው። ለእርሱ አሁንና ለዘላለም ክብር ይሁን! አሜን።

አብረው የታተሙ ትናንሽ መጽሐፍት

የእውነተኛ መለወጥ ሰባቱ እርግጠኛ ምልክቶች

በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ እርግጠኛ መለወጥ መከናወኑን እናም ያ ሰው በእርግጥ በጌታ መሆኑን ለማወቅ የሚጠቅሙ የሕይወት ለውጥ ማስረጃዎች ይኖራሉን? አንድ ሰው መለወጡን እንዴት እናውቃለን? ይቺ ትንሽ መጽሐፍ መለወጣቸውን በመጠራጠር ለሚቸገሩና እነሱንም ለመርዳት በማማከር ለሚያገለግሉ መምሪያነት የምትጠቅም ናት።

ሁሉ ከንቱ ትርጉመ ቢስ

ንጉሱ ሰለሞን፣ ደስታን ሊሰጡ ይችላሉ የሚባሉትን ነገሮች ሁሉ ከፈተነና ከመረመ ረ እንዲሁም ካየ በኋላ ሁሉ ነገር ከንቱና ትርጉም የለሽ መሆኑን ተረድቷል። ስለዚህም ሰዎች ጌታን ፈልገው ካላገኙ እንዲሁም በሕይወታቸው የጌታን ምህረት ኃይሉንና ምሪ ቱን ካልተለማመዱ በስተቀር ሁሉ ነገር የተለመደና ጥቅም የሌለው እንዲሁም ትርጉመ ቢስ መሆኑን ተናግሯል። በዚህ እውነታ ላይ በመመሥረት ይቺ መጽሐፍ ሰዎች በጊዜ ወደ ጌታ እንዲመለሱ ታሳስባለች።

በቅርቡ የሚታተሙ መጽሐፍት

የነፍሶች ሐኪሞች

የወንጌል አገልግሎት

በአሁኑ ጊዜ ኃጢአተኝነትን አሳምኖ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ማዳን ለሞቱት ነፍሳት የሚገልጥ ስብከት ብዙ አይሰማም። በመሆኑም በኃጢአት ለወደቅነው ለእኛ ለሰው ልጆች ከተሰጡን ሁሉ እጅግ የላቀው ጥበብ የወንጌል ስብከት ጠፍቷል ለማለት ይቻላል። ስለዚህም ጸሐፊው ለአሳማኝ የወንጌል ስብከት የሚያገለግሉ ጥቅሶች እንዴት እንደሚመ ረጡ እና ለስብከት እንዴት እንደሚዘጋጁ ያሳያል። ከዚህም በተጨማሪ የዘመናዊውን የቤተክርስትያን ዕድገት እንቅስቃሴዎች ስጋዊ ቴክኒክ እየነቀፈ ከሁሉ የሚበልጠውን ታላቅና ቀጥተኛ የወንጌል ስብከት አገልግሎትን ጠቀሜታ ያብራራል።

የባፕቲስት አቋመ እምነት

አጥቢያ ቤተክርስትያን እራሷን የቻለች መሆኗን የሚያምኑ የባፕቲስት ታላላቅ አገልጋዮች በ1644 ባደረጉት ጉባኤ የመጀመሪያውን የባፕቲስት አቋመ እምነት አዘጋጁ። በዚህ ላይ ተመስርቶ በ1689 በለንደን በተደረገው ሁለተኛው ጉባኤ ይህ ባለ 32 አንቀፅ አቋመ እምነት ተዘጋጀ። ይህ አቋመ እምነት በቅዱስ ቃሉ ላይ የተመሠረተና ለክርስትና እምነት እውነተኛና የጠራ ዶክትሪን መሠረት ነው።

የሰንበት ትምህርት ቤትን ጀምሮ ማሳደግ

ይህ ተግባራዊ ማንዋል የሚመጣውን ትውልድ በወንጌል እውነት ለማሳደግ የሚረዳ የሰንበት ትምህርት ቤትን እንዴት መጀመር መምራትና አሳድጎ ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል።

ትምህርት ለሕይወት
የአራት ዓመት ተከታታይ የሰንበት ትምህርት መጽሐፍ (መጽሐፍ 1 - 4)
በአራት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የሚሰጡና ወንጌል ተኮር በመሆን በአስደናቂ ሁኔታ የተዘጋጁ ተከታታይ የሰንበት ትምህርት መጽሐፍት::

በአማርኛ በቅርብ ስለሚታተሙት መጽሐፍት በተጨማሪ ለማወቅ ከፈለጉ የሚከተለውን አድራሻ በመጠቀም በጽሑፍ ሊጠይቁን ይችላሉ: -

Email:- books@wakemantrust.org

እንደዚሁም በመላው ዓለም ውስጥ በዌብ ሳይት የሚተላለፈውን የዶ/ር ፒተር ማስተርስን ስብከት ለመቅዳትና በነፃ ለማዳመጥ የሚፈልጉ ከሆነ በሚከተለው ዌብ ሳይት ለመጠቀም ይችላሉ: -

www. Metropolitan Tabernacle.org